## መሥዋዕትነት ከቤተ ክርስቲያን ፡

በኢትዮጵያና በግብፅ ቤተ ክርስቲያን መካከል ያለው ስለ ጳጳሳት ሹመት ነገር ከዚህ በፊት እንዳሳየነው ይህን በመሰለው የስምምነት ና የመግባባት መንገድ ወደ መልካም ፍጻሜ ከደረሰና የእስክንድርያውም ፓትርያርክ ኢትዮጵያን ጐብኝተው ከተመለሱ በኋላ፤ ጳጳሳቱ ወደ የተሾሙበት ሀገረ ስብከታቸው እየሔዱ የተመረጡበትን መንፈሳዊ ተግባር በትጋትና በንቃት ሆነው ያከናውኑ ጀመር ። ሕዝቡም በፍትሐ ነገሥት ውስጥ በማይ ገባ የተጻፈውን ፤ ወሰብአ ኢትዮጵያ ኢይሚሙ እማዕምራኒሆሙ የተባለው መጽሐፈ ዕዳ ተፍቆከተ ወላጆቹ ጳጳሳት በማግኘቱ እጅግ ደስ ብሎት ነበር ።—

የጳጳሳቱም ስምና ሀገረ ስብከት ቀጥሎ የተመለከተው ነበር ።

ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ ሸዋንና ሐረርን ይዘው ሊቀ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ።

ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ የኢትዮጵያ ምሥራቅ ጳጳስ ።

ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ የመንበረ ተክለ ሃይማኖት ጳጳስ ።

ብፁዕ አቡነ ሚካኤል የኢሉባቦርና የከፋ ጳጳስ ።

ብፁዕ አቡነ አብርሃም የጐጃምና የጐንደር ጳጳስ ።

ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ የትግሬ ጳጳስ ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከተወላጆቹ ጳጳሳት በማግኘቱ ከሚሰማው ደስታ በላይ ከጐጃምና ከጐንደር፤ከትግሬና ከኢሉቡር ከቀሩትም ከኢትዮጵያ አውራጃዎች ከሆኑት ሀገሮች ሁሉ ለክህነት የሚመጡት ሕፃናት ውሀ እየወሰዳቸውና አውሬ እየበላቸው በከንቱ ሞተው ይቀሩ ስለነበር፤ ይህ ችግር ተወግዶ ሕፃናቱም ሆኑ ሽማግሌዎቹ ከየደጃቸው ሥልጣነ ክህነትን ለማግኘት ስለቻሉ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በቤተ ክህነት በኩል ያደረጉትን ታላቅ ሥራ የማያደንቅና ፈጣሪውን የማያመሰግን አይገኝም ነበር ።—

ሥጋዊዉና መንፈሳዊዉ ሥራ እንዲህ ባማረ ሥነ ሥርዓት በመከናወን ላይ ሳለ ግፈኛው ጠላት ኢትዮጵያን ለመውረር ተነሣ፣ ስለሀገር መከላከልና ደምንማፍሰስ፣ ሕይወትን መሥዋዕት እስከ ማድረግ ለሀገር፣ ፀጥታ፣ ለሃይማኖት ክብር ፣ ከፍተኛ ግዳጅን መፈጸም ከልዑል እግዚአብሔር የተሰጠ ሕግ በመሆኑ ኢትዮጵያዊ የሆኑ ሁሉ በጸሎተ ሃይማኖት መልካም ሥነ ምግባር የአባቶችን ዓላማ ተከትሎ ለሀገሩ የሚያስፈልገውን ሁሉ እንዲያደርግ፣ ጳጳሳትም ቀሳውስትም ለሕዝቡ ጠቅላላ ትምህርትና ምክር ሰጡ። የጠላትም አሳብ እየገፋ ሔደ፣ ወረራ ስለተጀመረ የቀሩት ጳጳሳት በያገረ ስብከታቸው ሆነው ሕዝቡን እንዲያበረታቱ ሲደረግ የምሥራቅ ኢትዮጵያ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ፣ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር አብረው ወደ ሰሜን የጦር ግንባር ዘመቱ ፣ ጦርነቱ ግን ፤ ሕዝቡ በ ማያውቀው በመርዝ ፈ ሳ ሽ፣ በጋዝ ጭስ ፣ በቦምብ በመሆኑ ምክንያት በወታደር ብቻ ሳይሆን ሴት ወንድ ሕፃን ሽማግሌ ሳይለይ ሰው እንስሳ ሳይመርጥ በጠቅላላው በሕዝቡና በአገሪቱ ላይ ጽኑ አሠቃቂ አደጋ አደረሰ ።

ንጉሠ ነገሥቱም እንደ አንድ ወታደር በጦር ሜዳ ከተዋጉና ለሕዝባቸው ከተከላከሉ በኋላ፤ እግዚአብሔር በቸርነቱ ሕይወታቸውን ከአደጋ ስለ ጠበቀው በጸጸሳቱና በእጨጌው በመሳፍንቱና በሊቃውንቱ ልመና ጦርነቱ በለተወጠ አቅድ እንዲከናወን ስለተደረገ ግርማዊነታቸው በጀኔብ ጉባኤ የኢትዮጵያን ሕዝብ አቤቱታ ለማቅረብ ሲሔዱ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ከሰሜን የጦር ግንባር ተመልሰው ደብረ ሊባኖስ ገቡ ከዚያም ኢትዮጵያውያን አርበኞች በለሀገራቸው በሚያደርጉት ሕጋዊ ትጋድሎ የመንፈስ መሪ ሆነው አዲስ አበባ ገብተው አስደናቂ በሆነ የመንፈስ ብርታት ሥርዓተ ሃይማኖትን ስለ ሀገር ስለንጉሠ ነገሥት ስለ ቤተ ክርስቲያን ስለወገን ስለታሪክ ክብር ሕይወትን መሥዋዕት ማድረግ ሕጋዊ የተቀደሰ ሥራ መሆኑን በጠላት ሹማምንት በብዙ ሕዝብ መካከል አረጋግጠው ካስተማሩ በኋላ ሐምሌ ፳፪ ቀን ፲፱፻፳፰ ዓ ም ከኔሮን ተከታዮች የሰማዕትነት ጽዋ ተቀብለው ቅዱስ ጴጥሮስን በስምና በግብር መስሉት ፤

ከጥቂት ጊዜ በኋላም በጥቅምት ወር ፲፱፻፳፱ ዓ ም ብፁዕ አቡነ ሚካኤል የሐዋርያነት ጽዋቸውን ተቀብለው የሰማዕትነትን ግዳጅ ፈጸሙ ።

ከአምስት ዓመት በኋላ እግዚአብሔር በግፍ የፈሰሰውን የኢትዮጵያን ደም ተቀብሎ የኢትዮጵያን ነፃነት ሲመልስ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በድል አድራጊነት ወደመናገሻ ከተማቸው ከገቡ በኋላ የብፁዕ አቡነ ጴጥሮስን ሐውልት በሐምሌ ፳፪ ቀን ፲፱፻፴፫ ዓ ም ስምከ ሕያው ዘኢይመውት ብለው መርቀው አቆሙ ።

በምርቃቱ ጊዜ የተደረጉ ንግግሮች

የብፁዕ እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ንግግር ።

ንወድሶሙ ለዕደው ክቡራን አበዊነ አባ ጴጥሮስ ወአባ ሚካኤል ጳጳሳቲነ ሢራክ ተበኢስ በእንተ ጽድቅ እስከ ለሞት ያለውን ቅዱስ ጳውሎስም ጺሐፍኩ ለክሙ ከመ ኢትደመሩ ምስለ ዘማውያን ወኢኮ ዝሙተ ዝ ዓለም ባሕቱ ሀለው ዓዲ መስተአግላን ወሐያድያን ወእመ አኮሰ ይደልወክሙ ትፃኡ እምዝንቱ ዓ ለ ም ያለውን ይዘው ሕገ እግዚአብሔርን ከማይሰማ የሰው አገር ከሚቀማ ከግፈኛው ጠላታችን ጋራ አንድ አንሆንም ብለው ደማቸውን ያፈሰሱ ፤ ከዚህ ዓለም የፈለሱ አባቶቻችንን አቡነ ጴጥሮስንና አቡነ ሚካኤልን ልናከብራቸውና ልናመሰግናቸው ይገባናል ። ይኸውም ስለሀገር ነፃነት መሞታቸው ከቅዱሳን ሞት የተያያዘ ነው እንጂ ከንቱ አይደለም ፤ ፩ኛ ሙሴ ከግብፃውያን ጋራ ተድላ ደስታ ከማድረግ ከእሥራኤል ጋራ መከራ መቀበል ይሻለኛል ብሎ መከራ ተቀብሏል ፤ ፪ኛ ኤልያስ ስለናቡቴ ርስት ከኤልዛቤል ተጣልቶ ተሰዱዋል፤ በዚህም ቀናኢ ለሕገ አምላኩ ተብሎ ተመስግኖበታል ። ፫ኛ መጥምቀ መለኮት ዮሐንስ ሔሮድስን ሃይማኖት ሳይሆን ዋርሳ ወረስህ ሕገ እግዚአብሔርን አፈረስህ ብሎ ቢዘልፈው በሰይፍ ተመትቶ ሞቷል ። ፬ኛ ዮሐንስ አፈወርቅ አውዶክስያ የምትባል ንግሥት ያንዲት ድኃ ሴት ርስት ብትቀማ መልሺ ርስቷን አላት ፤ አይሆንም አለችው ፤ አወገዛት ፤ በዚህ ምክንያት በደሴተ ጋግራ ታሥሮ ተግዞ ሞቷል ብለው ጨረሱ ።

ከዚህ በኋላ ግርማዊ ጃንሆይ ወደ ሐውልቱ ሔደው የአበባ አክሊል በሐውልቱ ላይ አኖሩ ፤ ወዲያው ለብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ የክብር ሰላምታ ሰጥተው ከዚህ በታች ያለውን ቃል ተናገሩ ።—

## የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ንግግር ።

ከዛሬ አምስት ዓመት በፊት ጭንቅና ሥቃይ እየታየ የሰውን ልብ እንደ ጦር በሚ ወጋ ኃዘን በተዋለበት ቦታ ለተሰበሰበው ሕዝባችን ስንናገር ፥ የደስታና የኃዘን አሳብ ለእኛ እንደሚሰማን ፤ ለሁላችሁም መሰማቱ እርግጥ ነው ።—

ሰው ለደኅንነቱም ፤ ለጥፋቱም ምክንያት ሆኖ ሕይወቱ በሚገኝበት ዘመን ይነስ ይደግ እንጂ ፥ ሲያንስ በገንዘቡ በጉልበቱ ፥ ሲበዛ በሕይወቱ በመሥዋዕትነት እስከ መሰ ጠት ሲደርስ የሚታይ ነው ፥

በሁለቱም ረገድ የሚሰጠው መሥዋዕትነት ለሚገምት ልብ አሳዛኝ ሳይሆን ኢያልፍም ፤ ለደኅንነትም፤ ለጥፋትም የሚሰጥ መሥዋዕትነት አሳዛኝ ስለ መጀመሪያው የሚደረገው በጎ ፈቃድን በመግዛት ስለሆነ ከዕለት ጠቃሚነቱ በቀር ለትውልድ ኩራት ለታሪክ ገናናነት የሚሰጥ ነውና ይህንን ለመመልከት ለበቃ ፥ ኃዘኑ በደስታ የሚለወጥ በመሆኑ ኃዘንም ደስታም ይሰማናል እሰኘን ።—

የዛሬ አምስት ዓመት በዚህ ቀን የኢትዮጵያ ምሥራቅ ጳጳስ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ለግፈኛው ጠላት አትገዙ ፥ ስለነፃነታችሁ ተከላከሉ ፤ ነፃነታችሁ ከሚረክስ ሙታችሁ ስማችሁ ቢቀደስ ታላቅ ዋጋ ያለው ክብር ታገኛላችሁ ብለው በአርበኞቻችን መካከል ሆነው ስላወገዙ የፋሽሽት መንግሥት ወኪል ጨካኙ ጄኔራል ግራዚያኒ በዚሁ ቦታ በመትረየስ አስደበደባቸው ።—

ኢትዮጵያን ለመውረር መጥቶ የነበረው ፋሽሽት በሙሉ ዓለም የሕዝባችንን ስም ሲያጠፋ ጨካኝና ግፈኛ እያስመሰለ ሲሰብክ ነበር ። ከኢትዮጵያውያኖችና ከኢጣ ልያኖች ግፈኛና ጨካኙ ይታወቅ ዘንድ በዓለም ፍርድ ቤት ሊመዛዘን ቻለ ። ሁለቱም ወገኖች የተፈተኑባቸው ዓመታት በቅርብ አለፉ ። ይህም የዛሬው ቀን መታሰቢያ አን ደኛው ዋና ምስክር ነው ።—

የብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ፥ የመጨረሻው ትንፋሻቸው ፤ የኢትዮጵያ መሬት ጠላትን ብትቀበይ የተረገምሽ ሁኚ ፥ ሲል ሞታቸውን ባረከ ። ይህም የማይሞት ቃል እስከ ምጽ አት መምህር ነው ። ይህንንም ሕያው የሆነ ቃል ተናግረው ወደ ተጠሩበት ሠርግ ቤት ለመሔድ የሰማዕትነት ጽዋቸውን ተቀበሉ ፥

ኢትዮጵያም የብፁዕ አቡነ ጴጥሮስን የመጨረሻ ውግዘት አክብራ ለአደራ የበ ቃች ሆና ተገኘች ። በዕረፍት ከተቀበለቻቸው ልጆቿ በቀር ፥ እነሆ ጠላቷን አስወጥታ የተበታተኑትን ልጆቿን ሰብስባ በዕልልታ በደስታ ተቀበለች ።—

በዚህ ቦታ የፈሰሰው የብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ንጹሕ ደም አለማቋረጥ ስለነፃነት ሲጮህ ቆይቶ ዛሬ መበቀሉን አየን ።—

« ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ደማቸው በብዙ ወገን አፍርቷል ።
ነፍሳችሁን ለመግደል አይችልምና ሥጋችሁን ከሚገድል አትፍሩ ያለውን የወንጌልን ቃል ተከትለው ሞትን በመናቅ፥የጨካኞችን ግርማ ባለመፍራት የጻድቅ ሞታቸውን ሕይ ወት በማድረጋቸው የተከተሏቸውና ስለሀገራቸው የተሠው ጀግኖች ቊጥራቸው እጅግ ብዙ ሆነ ፤ የነርሱንም መታሰቢያ የምንዘነጋው አይደለም ።

አምስተኛ መምህር ጌታሁን የእቲሳ ገዳም መምህር ናቸው፤ መዓርገ ጵጵስናውን ከተቀበሉ በኋላ ጥንታዊው የተጸውዖ ስማቸው ተለውጦ

ብፁዕ እጨጌ ገ/ጊዮርጊስ ፡ ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ
መምህር ገሪማ ብፁዕ አቡነ ሚካኤል
ሊቀ ሥልጣናት መልእክቱ ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ

መምህር ዘፈረ ብርሃን ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ ።
መምህር ጌታሁን ብፁዕ አቡነ ጢሞቴዎስ ተብለዋል ። ከዚህ በኋላ ከ፲፱፻፴፬ ዓ ም እስከ ፲፱፻፵ ዓ ም ድረስ ከግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፤ ከእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያንና ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በየጊዜው የተጻፉትን መልእክቶች እንዲሁም የጉዳዩን መነሻና መድረሻ ለመግለጥ ከመልእክቶቹና በጊዜው ከነበሩ ጸሐፍት የተሰጡትን አንዳንድ አስተያየቶች እንመለከታለን ።

## ክፍል ፲፰
### የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ መብት ጉዳይ እንደገና ስለመነሣቱ ።

በጣላት ወረራ ዘመናት በኢትዮጵያ በብዙ ወገን ችግር መድረሱ የሚታወቅ ነው ፡ ይልቁንም ግብጻዊው ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ቄርሎስ በኢትዮጵያ የተሰጣቸውን መንበራቸውን ትተው በሥራቸውም ኢትዮጵያዊዉን ጳጳስ አቡነ አብርሃምን ወክለው ስለሔዱ በቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ ትልቅ ችግር ደረሰ ፤ ከአምስቱ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ሦስቱ በሞት ተለይተዋል ፤ ሁለቱ ብቻ በሕይወት ቀርተዋል ፤ ይህም ጠላት አዲስ የመንፈሳዊ ወረራ እንዲጀምር አደገኛ ምክንያት ነበር ፡ ይህን የወረራ ፅንስ ለማጨናገፍ በመከራው ዘመን የነበረው መንፈሳዊ ጉባኤ አቡነ አብርሃምን ሊቀ ጳጳሳት አድርጎ ሕዝቡን እያበረታታ ከየአቅጣጫው የሚሠነዘረውን የጠላት ወረራ በመንፈስም በሥጋም በመከላከል ላይ ሳለ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በድል አድራጊነት ገቡ።

አዲሱ አመራር ሲጀመርም በ፲፱፻፴፬ ዓ ም የእስክንድርያው ፓትርያርክ አቡነ ዮሐንስ በግብፅና በኢትዮጵያ የነበረውን ግንኙነት ለማደስ በመልእክት ጥያቄ አቀረቡና ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መልስ ተሰጥቷቸው ሳለ ውጤቱ ከመታወቁ አስቀድሞ ግብጻዊውን ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ቄርሎስን ሌሎችን መልእክተኞችም ጨምረው ላኩ ። ከመልእክተኞችም ጋር ንግግር ከተደረገ በኋላ መልእክተኞች ሲመለሱ አቡነ ቄርሎስ ከዚሁ ቀርተው ነበርና ተፈቅዶላቸው ወደ መንበረ ሊቀ ጳጳሳቱ ገቡ ። ወዲያውም ፓትርያርኩ አቡነ ዮሐንስ ስለ አረፉ ሌላው ፓትሪያርክ እስኪመረጥ ጉዳዩ ረዥም ጊዜ ከወሰደ በኋላ በ፲፱፻፴፮ ዓም የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መልእክተኞች ወደ ኢትዮጵያ ስለመጡ በግብጽ መልክተኞችና በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መልክተኞች መካከል ንግግር ተጀመረ ፤ በንግግሩም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መልእክተኞች ለኢትዮጵያ ከተወላጆችዋ ሊቀ ጳጳሳት እንዲሾምላት እሱም ጳጳሳትን እንዲሾም እንዲፈቀድለት በማለትና ሌላውንም አስፈላጊ የሆነውን ነገር በመግለጥ ቀደም ብሎ የላኩት መልክት ምን ውጤት እንዳገኘ ጠየቁ ፤ ግብፃውያኑም ለቀደመው ልዩ ልዩ ምክንያት ሰጥተው አሁን ወደ ውይይቱ ለመግባት ፈቃደኞች መሆናቸውን ከገለጡ በኋላ በውይይቱ ኢትዮጵያዊው ሊቀ ጳጳሳት ይሾም በማለት ፈንታ አማርኛ የሚያውቅ ግብጻዊ

በኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስነት ተሹሞ ከኢትዮጵያ ውያን ጋራ የሁለቱ አገሮች አንድነት ተጠብቆ ችግሩ የሚቃለል መሆኑን ገለጡ፤ ኢትዮጵያውያን ግን ኢትዮጵያዊው መን ፈሳዊ መሪ የኢትዮጵያ ተወላጅ መሆኑ በመከራና በሰላም በኃዘንና በደስታ ጊዜም ቢሆን ሕዝቡን በልዩ ልዩ መንገድ የሚረዳ መሆኑን ገልጠው የስማዕታቱን የነ አቡነ ጴጥሮስን፣ የነ አቡነ ሚካኤልን የሌሎችንም አበው ታሪክ እየጠቀሱ ካስረዱአቸው በኋላ የሁለቱ አገሮች አንድነት በሃይማኖት አንድነት ተጠብቆ የኢትዮጵያ ተወላጅ ሊቀ ጳጳሳት በእስክንድርያው ፓትረያርክ እንዲሾም ቢሆን የሚያስቸግር ነገር አለ መኖሩን አስረዱ። ግብፃውያኑ ግን የተለመደውን አሳብ ባለመለወጥ በእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ማኅበርና የኒቅያ ጥቅስ ነው በሚባለው የሥርዋፅ ቃል አመካኙ፤ ኢትዮጵያው ያኑም የኒቅያ ጉባኤ ከ፲፱፻፳፭ ዓ ም በፊት የተደረገ ስለሆነ ግብጽና ኢትዮጵያ ባንድ ኦርቶ ዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት በቅዱስ ማርቆስ አባትነት የሚተባበሩ ሲሆኑ ኢትዮጵያው ያን እንኳን በኢትዮጵያ እንዳይሾሙ የሚያደርግ በእስክንድርያ መንበረ ፓትርያርክም ቢሆን በፓትረያርክነት ከመሠየም የሚያግዳቸው ነገር አለመኖሩን ግልጥ አድርገው አስ ረዱ ወደፊትም ቢሆን የግብጽና የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች በሃይማኖት የማይለያዩ ወን ድማማቾች ስለሆኑ መብታቸው ተጠብቆ በፓትርያርኩ ምርጫ እንዲገኙ ጠየቁ፤ ስለ ኒቅያ ጥቅስም በኒቅያ ጉባኤ የተሰጠው ውሳኔ በሌሎችም አብያተ ክርስቲያናት የሚ ገኝ ስለሆነ መታየት እንደሚገባው ገለጡላቸው፤ ግብጻውያኑም የኢትዮጵያን ቤተ ክርስ ቲያንን ጥያቄና አሳብ ለእስክንድርያው ፓትረያርክ እንደሚያስረዱ ካረጋገጡ በኋላ ውይ ይቱ ተፈጽሞ ሰኔ ፲፩ ቀን ፲፱፻፴፯ ዓ ም የኢትዮጵያ መንፈሳዊ ጉባኤ አንድ ውሳኔ ለብፁዕ አቡነ መቃርዮስ አስተላለፈ።

የኢትዮጵያ መንፈሳዊ ጉባኤ በሰኔ ፲፩ ቀን ፲፱፻፴፯ ዓ ም ለብፁዕ አቡነ መቃርዮስ የላከውና ፯ ጥያቄዎች የተመለከቱበት ደብዳቤ።

መንፈሳዊ ጉባኤ ዘመንግሥተ ኢትዮጵያ
የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣኖች ለብፁዕ አባታቸው ለሊቀ ጳጳሳት አቡነ መቃርዮስ የትሕትና ሰላምታቸውን እያቀረቡ በቅዱስ ማርቆስ መንበር ተቀም ጠው ይባርኳቸው ዘንድ ስለተመረጡ፤ ደስታቸውን ይገልጣሉ።—

ከዚህ በኋላ ቀጥሎ ያለውን አሳብ ሲያቀርቡ ብፁዕ አባታቸው አቡነ መቃር ዮስ በነገሩ በጣም እንዲያስቡበትና መልካም ፍጻሜ እንዲያስገኙለት ተማምነው ነው።

ብፁዕ አባታችን ሆይ፤

ኢትዮጵያ በፋሽሽት መንግሥት በተወረረችበት ሰዓት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲ ያን ከእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ተለይታ እንድትኖር በጠላት የተመሠረተ አሳብ መሆኑ ታውቋል።

በፊተኞችም ዘመናት ውስጥ በኢትዮጵያ ላይ የጦር አደጋ በደረሰ ቁጥር የኢት ዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ጋራ መገናኛዋ እየተቋረጠባት የመከራው ዘመን እስኪያልፍ ድረስ ራስዋን ችላ መኖርዋ የታወቀ ነው፤ የመከራውንም

ዘመን በሃይማኖቷ ጸንታ ወደ ሰላሙ ዘመን በደረሰች ቍጥር ከማርቆስ መንበር ላይ የተቀመጠውን አባቷን ከመፈለግ አቋርጣ አታውቅም ፤ አሁንም ወደፊት ያላት ምኞት ይኸው መሆኑን ስትገልጽ ደስ ይላታል ።—

ይሁን እንጂ ፤ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መብት ባለማግኘቷ ምክንያት በኢትዮጵያ ላይ አደጋ በመጣ ቍጥር ለክርስቲያን የሚገባውን ሥርዓት ሁሉ የኢትዮጵያ ምዕመናን ለማድረግ አልተቻለም ። በዚህም ምክንያት ወደሌላ ሃይማኖት የሔዱና የሌላውን ሃይማኖት ባህል የለመዱ ብዙ ኢትዮጵያውያን ናቸው ።

ስለዚህ ፤ ወደፊት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የቅዱስ ማርቆስን አባትነት ሳትለቅ ሃይማኖቷ የሚጸናበትንና ምእመናኖችዋም የሚጠቀሙበትን መንገድ ለመመሥረትና ለመከተል ግዴታ እንዳለባት ስለተገነዘበች ፥ የሚከተሉትን መብቶች ፤ እማርቆስ መንበር ላይ የተቀመጡት ቅዱስ አቡነ መቃርዮስ ባርከው እንዲሰጧት ትለምናለች ።—

፩ኛ / ከኢትዮጵያ ተወላጆች ውስጥ በቤት ክህነት ክፍል አድገው ፤ በሃይማኖት ጸንተው ከሚኖሩት ከመንፈሳውያን አባቶች ለሊቀ ጳጳስነት የሚገባው ሰው ተመርጦ በእስክንድርያው አባታችን ተባርኮና ተቀብቶ እንዲሾምላት ።—

፪ኛ / የእስክንድርያው ሲኖዶስ በሚመርጥበት መሠረት የኢትዮጵያም ሲኖዶስ ለጵጵስና ለኤጲስ ቆጶስነት የሚገቡትን መንፈሳውያን አባቶች እንዲመርጥና ከእስክንድርያ አባታችን ተቀብቶ የመጣው ሊቀ ጳጳስ ባርኮ እንዲሾማቸው ።—

፫ኛ / በማርቆስ መንበር ላይ የሚቀመጠው አባታችን በሚመረጥበት ጊዜ የቅዱስ ሲኖዶስ በር ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ክፍት እንዲሆንና መልእክተኞችዋ በምርጫው ውስጥ እንዲገኙ ።—

፬ኛ / የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዘወትር በእስክንድርያው ቅዱስ ሲኖዶስ ውስጥ መንበር እንዲኖራትና ሲኖዶስ በተሰበሰበ ቍጥር መልእክተኞችዋ በሚገባቸው ደረጃ ተቀምጠው እንዲገኙ ።—

፭ኛ / ኢትዮጵያ በውድ ሳይሆን በግድ በጦር ኃይል ከእስክንድርያ ጋር እንዳትገናኝ ተከልክላ በተቋረጠችበት ጊዜ በሃይማኖቷ ጸንታ ወደ ሰላም ዘመን እስክትደርስ መርጣ የሾመቻቸውን ጳጳሳት ከግዝቱ እንዲፈቱላት ።—

፮ኛ / በኢትዮጵያና በእስክንድርያ መካከል ያለው የመንፈሳዊ ግንኙነት አሁን ካለው የበለጠ እንዲሆን የእናትነትና የልጅነትም መሠረት የጠነከረ ሆኖ እንዲኖር የገዳም ትምህርት ቤት በአዲስ አበባ እንዲከፈት ፥ ስለዚሁም ተማሪ ቤት አቋቋምና አካሔድ ቅዱስ አባታችን አቡነ መቃርዮስ ቅዱስ ቡራኬያቸውን እንዲሰጡን ፥ ከዚህ ተማሪ ቤት ተመርቀው ለጵጵስና ወይም ለቁምስና የታጩት መምህራን በምሥር ገዳማት ውስጥ እየሔዱ ከወንድሞቻቸው ጋራ በመንፈስ ተባብረው እንዲመለሱ ፥ እንደዚሁም ከምሥር የሚመጡት ወንድሞቻችን በኢትዮጵያ ገዳም ውስጥ ሲመጡ በመንፈሳቸው ሁሉ የተባበሩ ወንድሞች አግኝተው እንዲመለሱ ።—

ከዚህ በላይ በስድስቱ አንቀጾች የተመለከቱት ጉዳዮች ለእስክንድርያና ለኢትዮጵያ አንድነት ዘለዓለማዊ መሠረት መስለው የሚታዩ ናቸው ። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እንደሌሎቹ ኦርቶዶክሳውያን ብቸኝነትን አትፈልግም ፣ ከእስክንድርያ ጋራ በአንድነቷ ጸንታ ለመኖር ስለፈለገች ነው ፤ መለያየት የሚያመጡትን ምክንያቶች ሁሉ ለማስወገድ የወደደችው ።—

እነዚህን በስድስቱ አንቀጾች የተመለከቱትን ጉዳዮች የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አስፈላጊ ሆኖባት የጠየቀችበት ምክንያት ፣ ከብፁዕ አባታችን ተልከው ከመጡት ሰዎች ጋራ በተደረገው ጉባኤ የንግግር ማስታወሻ ውስጥ ይገኛል ።—

ይልቁንም በአንደኛው ና በሁለተኛው አንቀጽ ውስጥ የተመለከቱት ዋናዎቹ ጥያቄዎች ፣ ለቀድሞ ጊዜ አስፈላጊ አይደሉም ተብለው ተደንግገው እንኳን ቢሆን የዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድ መንፈስ በፍጹም አልተቀበለውም ።—

ስለዚህ ፣ ብፁዕ አባታችን አቡነ መቃርዮስ የአሳባችን ተካፋይ ሆነው የኢትዮጵያንና የእስክንድርያን መሠረት ለማናወጽ የተነሡትን ነፋሳት በተሰጣቸው በታላቁ ረድኤት ለማስወገድ እንዲደክሙበትና እንዲችሉ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አጥብቃ ታሳስባለች ።—

እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ

ዘነበረ በመንበረ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ።

ይህንንም ደብዳቤ የእስክንድርያ ዓቢይ መንፈሳዊ ጉባኤ ሲመረምረው ቆይቶ ከብዙ ጊዜ በኋላ በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በኩል ቀጥሎ የተመለከተውን ቃል አስተላለፈ ።—

የእስክንድርያ ፓትሪያርክ በየካቲት ፳፪ ፲፱፻፴፮ ዓ ም /፩—፫—፵፬/ የጻፉት ደብዳቤ ።

ካይሮ ፳፪ አምሺር ሺህ ፮፻፷
/የካቲት ፳፪ ቀን ፲፱፻፴፮/

በጣም ለተወደዱ ልጃችን ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ።

ቡራኬያችንን እየሰጠንዎ እንደዚሁም ከፍ ላለው ሰውነትዎና ለተባረኩት ልጆቻችን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጸሎታችንን ለእግዚአብሔር እናቀርባለን ።—

በእኔ ሰብሳቢነት የተሰበሰበው የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ሊነካ የማይቻለውን የቤተ ክርስቲያንን ሕግና ልማድ መሠረት አድርጎና እንደዚሁም በእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ና በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መካከል ያሉትን መገናኛዎች ለማጽናት ዋና አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች መሠረት አድርጎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ሁሉ በታላቅ ጥንቃቄ መርምሯል ።—

ምርመራ ባደረግን ጊዜም በተለይ የተመለከትናቸው አንዳንድ ጉዳዮች ስላሉ፣ ለነዚሁ ነገሮች ለግርማዊነትዎ መጻፍ አስፈላጊ ስለመሰለን ስለመጨረሻው ንግግር የኢትዮጵያን መልእክተኞች ለመጥራት እንድንችል ግርማዊነትዎ መልሱን በፍጥነት እንዲልኩልን እንለምናለን ።—

በተለይ የተመለከትናቸው ነገሮች እነዚህ ናቸው ።

፩ኛ / ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መልእክተኞች በሰኔ ፳፩ ፹፫ ዓ ም /፳፯ / ፯ / ፺፩ / ከቀረቡልን ጥያቄዎች መካከል አንዱ ጥያቄ አምስተኛው ነው ።—

ቃሉም የሚከተለው ነው ።—

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ጋራ ያላትን ግንኙነት የጦር ኃይል ቆርጦባት በነበረ ጊዜ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተገድዳ፣ሃይማኖትዋን ጠብቃ ለማኖር ስትል የመረጠቻቸው ጳጳሶች ውግዘት እንዲፈታ ።—

፪ኛ / እነዚህ ያለሕግ ከተቋቋመ ባለሥልጣን የመንፈሳዊን ሥልጣን በተቀበሉ ጊዜ የተወገዙት ጳጳሶች / አስኮፍ / ያላንዳች ውልና ያላንዳች ነገር መብት ከሌላቸው ሰዎች የመንፈሳዊን ሥልጣን በመቀበላቸው ማናቸውም ዓይነት የመንፈሳዊ ቅጣት ሳይ ደረግባቸውና ከነሱም ጳጳሶች ወገን መጸጸታቸውን ወይም ማዘናቸውን ሳይገልጹ ውግ ዘቱ እንዲፈታ ግርማዊነትዎ አስቀድሞም የቅዱስ ሲኖድን ጉባኤ ጠይቆ ነበር ። የቅዱስ ሲኖድ ጉባኤም በሰኔ ፲፱ ፲፱፻፹፬ / ፳፯/ ፯/ ፺፪ / ባወጣው ትእዛዝ እያንዳንዳቸው አስ ቀድሞ ያላቸውን ሥልጣን እንዲይዙ ተደርጎ እነዚህን ጳጳስ የተባሉትንያወገዘው ቃል እንዲፈታ አውጆ ነበር ።

፫ኛ / ከነዚሁ ከተባሉት ጳጳሶች / አስኮፍ / አብዛኞዎቹ አኳኋናቸውን ምንም ያል ለወጡ መሆናቸውንና ያንኑ ልብሳቸውን የጳጳስ ልብስ ለብሰው በዋናው ከተማ መቀ መጣቸውን ከአቡነ ኤልሙጥራን ጋራም ግንኙነት ያለማድረጋቸውን ሰምተናል ። ለኛ መታዘዛቸውን በሥራቸውም የመጸጸታቸውንና የማዘናቸውን ተግባር ለመፈጸም ይህም ቢቀር በነፍሳቸው ጥፋት ጊዜ የግዝቱን ቃል በመፍታት ስላደረገላቸው በጎ አድራ ጎት የቅዱስ ሲኖድን ጉባኤ ለማመስገን ከኛም ጋራ ግንኙነት አላደረጉም ።—

፬ኛ / ለነዚህ ሰዎች ስለተጠየቀው ነገር በጣም የተጣራ ነገር አልተመለከተም ። አሁን የሚጠየቀው / የምትጠይቁት / እነዚህ በሕግ ካልተቋቋመ ባለሥልጣን የመንፈ ሳዊ፤ ሥራ ሥልጣን የተቀበሉና በኋላም ከዚሁ ሥልጣን የተከለከሉ ሰዎች እንደ (አስኮፍ) እንዲቆጠሩና ደግሞ እንደገና አስቀድሞ ተሾመው ለነበሩት አገር እንዲሾሙ ነውን ።—

፭ኛ / እንደዚህ እንደሆነ ስለዚህ ነገር ለኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት የሚ ያስፈልጉትን ማለት በሀገሩና በልዩ ልዩ አውራጃዎች ያሉትን ገዳሞችና ቤተ ክርስቲ ያኖች በመመልከት የቤተ ክርስቲያን ጥቅሞች በተሻለ ደንብ የተጠበቁ እንዲሆኑ ሲደረግ የታሰበው አከፋፈልና የሚቋቋመውን ጠቃሚ ሥራ ማወቅ ዋና ነገር ነው ።

፮ኛ / ደግሞም እነዚህን ጥያቄዎች ያቀረቡልንን የቤተ ክህነት ሰዎች ለማወቅ በጣም እናስባለን ። እንደዚሁም እነዚሁ ሰዎች በሀገሩ ውስጥ የተቋቋሙትን የቤተ ክር ስቲያን አስተዳደር ክፍሎች ይልቁንም ገዳሞቹን የገዳሞቹን አለቃዎችና መነኰሴዎች እንደምን እንደሚያስተዳድሩ ለማወቅ እናስባለን ።—

፯ኛ / ደግሞም ለቤተ ክህነት ሥራ ከመመረጣቸው አስቀድሞ የእነዚህ ጳጳስ የተ ባሉትን የየአንዳቸውን ልዩ አኳኋን የሃይማኖት ትምህርታቸውንና የሃይማኖት ዕውቀ ታቸውን ደረጃ ወደ ጳጳስ / አስኮፍ / ደረጃ ሳይደርሱ አስቀድሞ የሠሯቸውን ልዩ ልዩ

ሥራዎች ፣ ይልቁንም የቤተ ክህነት ሰዎችና ሕዝቡም እንደምን እንደሚገምታቸው ለማወቅ እንፈልጋለን ።—

፫ኛ / ስለዚህ ነገር የሚመጡልንን መልሶች ካጠናን በኋላ የኢትዮጵያ ንና የቤተ ክርስቲያኗን ጥቅሞች ለመጠበቅ የሚችለውን ሁሉ መንፈስ ቅዱስ የሚያሳስበን አሳብ የሚሰጠን መሆኑን እናምናለን ። —

፬ኛ / አንዳንዶቹ የቀረቡት ጥያቄዎች ሳያቋርጥ አንድ ሺህ ስድስት መቶ ዓመት የቆየውን አኗኗርና አኳኋን ለመለወጥ ያመሩ ስለሆኑ ፣ በእነዚህ ጥያቄዎች ምክንያት ስለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ፍራታችንን እንድበቅዎትም ። እግዚአብሔር በዚሁ ጊዜ ሁሉ / ሺህ ስድስት መቶ ዘመን / ኢትዮጵያን ጠብቆ አድኗታል፣ ያለ ክርክር በ ነ ዚ ህ ባለፉት ዘመናት / ሺህ ስድስት መቶ ዓመት / የነበሩት ሰዎች በ አ ሁ ኑ ጊዜ ካሉት ሰዎች ያነሰ የተማሩና ለኢትዮጵያም ያነሰ ፤ የሚያስቡ አልነበሩም፣ደግሞም ስለኢትዮጵያ ሕዝብ ስለክብርዎና ስለእድገቷ ያለንን ጥልቅ የሆነ ፍቅራችንንና ታላቅ በጎ አድራጎታችንን ግርማዊነትዎ ያውቃል ።—

አምላካችን ከፍ ያለውን ሰውነትዎንና ግርማዊት እቴጌን ከንጉሠ ነገሥታዊ ቤተ ዘመድ ሁሉ ጋራ ጠብቆ እንዲያኖርልንና የታላቂቱን ኢትዮጵያ ሕዝብ የተባረኩትን ልጆቻችንን ሁሉ እንዲጠብቅልን እንለምናለን ።—

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትም ከፓትሪያርኩ የተላለፈላቸውን ቃል ጉዳዩን ለሚመለከተው ለኢትዮጵያ መንፈሳዊ ጉባኤ ከአስተላለፉ በኋላ ከ ዚ ህ በ ታ ች ያ ለ ው ን መልስ ለፓትሪያርኩ ላኩ ።—

ከግርማዊ ንጉሠ ነገሥት
ለብፁዕ የእስክንድርያ ፓትሪያርክ
በ፲፱ መጋቢት ፲፱፻፴፯ ዓ ም
የተጻፈ ደብዳቤ

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ
ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ
ለብፁዕነታቸው ሊቀ ጳጳስ ሣልሳዊ መቃርዮስ
የእስክንድርያ ፓትሪያርክ ።

ቅዱስ ጸሎትዎና ረድኤትዎ አይለየን እያልን ሰላምታችንን እናቀርባለን ። በመጋቢት ፩ ቀን እንደ አይሮፕ አቆጣጠር ፲፱፻፵፫ ዓ ም የጻፉልን ደብዳቤ ደርሶናል ። ለእኛና ለልጆቻችን ለሰጡን ቡራኬና ለሕዝባችንም ወደ እግዚአብሔር ለሚያቀርቡልን ጸሎት ምስጋናችን እንዲደርስዎ እንወዳለን ፡፤

የላኩልንም ወረቀት ለሚገባው ለመንፈሳዊ ጉባኤ አስተላልፈንለታልና ምላሹም በዚያው በኩል ይደርስዎታል ። ይኸው የተጀመረው የስምምነት መንፈስ እመልካም ፍጻሜ በፍጥነት እንዲደርስ ምኞታችን ነው ።—

መጋቢት ፲፱ ቀን ፲፱፻፴፯ ዓ ም ተጻፈ አዲስ አበባ ከተማ

የኢትዮጵያም መንፈሳዊ ጉባኤ በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በኩል የደረሰለትን የፓትረያርኩን መልእክት ከተመለከተ በኋላ ፡ ቀጥሎ የተጻፈውን መልስ ለፓትረያርኩ አስተላለፈ ።—

መጋቢት ፲፰ ቀን ፴፯ ዓ ም

የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት ፡—
ለብፁዕ አባታችን አቡነ መቃርዮስ

የእስክንድርያ ፓትረያርክ

ቅዱስ ቡራኬዎ ይደርሰን ዘንድ እየለመንን ሰላምታችንን በትሕትና እናቀርባለን ባለፈው ሰኔ ፳፩ ፲፱፻፴፮ ዓ ም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ምኞት በ፯ አንቀጾች ገልጠን ጽፈንልዎ ስለነበረ ስለዚሁ ጉዳይ ካሥር ወር በኋላ ወደ ግርማዊነታቸው የላኩትን መልስ አየነው ።

፩ኛ / የጠየቅናቸው ዋና ዋናዎቹ ጉዳዮች በአንደኛውና በሁለተኛው አንቀጽ ተመልክተው ሳሉ ብፁዕነትዎ ያሰበበት የማያስቸግረውን አምስተኛውን አንቀጽ ብቻ ይመስላል ። ይኸውም በአምስተኛው አንቀጽ ያመለከትንዎ ጥያቄ በጠላት ጊዜ ኢትዮጵያ ከእስክንድርያ ተቋርጣ በነበረችበት ዘመን ክርስቲያኑ ሕዝብ በሃይማኖቱ ጸንቶ እንዲኖር ላደረጉት መነኰሳት ውግዘቱ እንዲፈታላቸው ነው ። ውግዘቱ ይፈታላቸው ስንል ወደ ጵጵስና ሥራቸው ይመለሱ ብለን አልጠየቅንም ። ምክንያቱም ወደፊት ጳጳሳት የሚመካከሩበት ጉዳይ በመሆኑ ነው ፤ እስካሁንም ድረስ ከአባ ቄርሎስ ጋራ ግንኙነት እንዳያደርጉ ከናንተ ወገን በተጠየቅነው መሠረት እንደ ግዝት እንደ ተቀመጡ ናቸው ።—

ስለዚህ የጠየቅነው ጥያቄ በጽሕፈት የተላከልዎት ከመላክተኞችዎ ጋራ በሰፊው በቃል ከተነጋገርንና ከገባቸው በኋላ ስለሆነ በአራተኛው አንቀጽ በወረቀትዎ ላይ አሳባችንን እንዳልተገለጠ አድርገው በመመልከትዎ አዝነናል ። ብፁዕ አባታችን ከማንም የበለጠ ለቤተ ክርስቲያናችን ያስባሉ ብለን ስንመኝ በዚህ አስተያየት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያለችበትን ችግር ያልተመለከቱልን ና ለነገሩ በቅርብ ቀን መልካም ፍጻሜ ለመስጠት ያልታሰበበት መስሎ ታየን ።

በማንኛውም ረገድ የእኛ ጥያቄ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በመልካሙም ሆነ በመከራውም ሰዓት ምእመናኖቹዋን ያለችግር ጠብቃ ከእስክንድርያም ሳትለይ የምትኖርበትን አኳኋን ነው ያመለከትነው ።—

፪ኛ / በዚሁ በወረቀትዎ በ፪ኛው አንቀጽ ላይ ስለጠየቁን ጥያቄ የፊተኛውንም ያሁኑንም ወረቀት የጻፍንልዎ በመስከረም ፩ ቀን ፲፱፻፲፱ ዓ ም የቆመው ቅዱስ መንፈሳዊ ጉባኤ ነው ፡ በ፲፱፻፳፩ ዓ ም በግንቦት ወር አራቱ መነኰሳት ካይሮ ሔደው የጵጵስና ማዕርግ ተቀብለው የመጡት በዚሁ ጉባዔ መራጭነትና አቅራቢነት ነው ።—

ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ የእስክንድርያ ፓትሪያርክ በ፲፱፻፳፪ ዓ ም ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስን አዲስ አበባ ላይ አጳጵሰው የሔዱትም በዚሁ ጉባኤ መራጭነትና አቅራቢነት ነው ።—

በማናቸውም ረገድ ይህ ቅዱስ ጉባኤ የ፲፪ቱ አውራጃ የአብያተ ክርስቲያናት ወኪሎች ተመርጠው የተሰበሰቡበትና በብፁዕ እጨጌው መሪነት እንዲካሔድ በቤት ክህነታችንና በቤተ መንግሥታችንም የታወቀ ነው ።—

፫ኛ / ይኸው ቅዱስ ጉባኤ እስካሁን ድረስ በብፁዕነትዎ ወገን የቤተ ክርስቲያናችንን ችግር የሚያቃልልላት ነገር ባለመገኘቱ ምክንያት፥ ይልቁንም ከሐምሌ ወር ጀምሮ የዲቁናና የቅስና ሥርዓት እንዳይፈጸም ቤተ ክርስቲያናችን ስለተጨቆነች የእስክንድርያው ፓትሪያርክ ከነበሩት ከአቡነ ዮሐንስ ጵጵስና የተሾሙት አቡነ ይስሐቅ ለምእመኖቻችን የሚገባቸውን ሥራ ሲሠሩ እንዲቆዩ፥ ዲቁናና ቅስናንም እንዲሰጡ ፈቃዳችን ነውና ብፁዕነትዎ እንዲፈቅድልን እናመለክታለን ።—

፬ኛ / በወረቀትዎ በ፫ኛው አንቀጽ ለቀረበልን ጥያቄ እገሌ ይሾምልን ብሎ ጉባኤያችን ያቀረበው ስም ለጊዜው የለምና የመንፈሳዊ ዕውቀታቸውንና የችሎታ ደረጃቸውን ለማወቅ ዛሬ አስፈላጊ ጊዜ መስሎ አልታየንም ።—

ከዚህ በላይ ጉባኤያችን የገለጠው አሳብ ለጥያቄው በቂ ሆኖ ይገኛል ስንል እንመኛለን፥ ስለዚህ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ና የኢትዮጵያ ሕዝብ ለስምምነት ያለው መልካም መንፈስ ሳይበርድ በከንቱ ጊዜ የሚፈጁትን ጉዳዮች አስወግደው ለዋናው ጥያቄአችን በወረቀትዎ አርእስት እንደተመለከተው የመጨረሻው ንግግር የሚደረግበትን መንገድ በቶሎ አስበው እንዲያስታውቁን እናሳስባለን ።—

ሰላምታችንን በአክብሮት እያቀረብን ቡራኬዎን ደግመን እንለምናለን ።—

እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ
ዘነበረ በመንበረ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ።
መንፈሳዊ ጉባኤ የሰጠው ውሳኔ ፥

ስለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የቀረቡትን ጥያቄዎች የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት አባ መቃርዮስ ባሉበት ታላቁ የእስክንድርያ ዐቢይ ጉባኤ በ፲፱፻፴፯ ዓ ም በሰኔ ወር ታላቅ ጉባኤ አድርጎ አንድ በአንድ ተመለከተ ። የብዙ ጊዜ ክርክር ከተደረገባቸውም በኋላ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያቀረበቻቸውን ጥያቄዎች አንዳንዶቹን የሚያጸድቅና የሚቃወም ውሳኔ ሰጥቶ ለኢትዮጵያ መንፈሳዊ ጉባኤ አስተላለፈ ።—

የኢትዮጵያ መንፈሳዊ ጉባኤ ከእስክንድርያ መንፈሳዊ ጉባኤ የተላከለትን ውሳኔ ላቀረበው ጥያቄ ሙሉ የሆነ መልስና ትክክለኛ ውሳኔ ሆኖ ስላልተመለከተው ቀጥሎ የተመለበተውን የውሳኔ ማስታወቂያ ለንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ገለጠ ።—

የእስክንድርያ መንፈሳዊ ጉባኤ ውሳኔ አድርጎ የሰጠው ትእዛዝ ።

ከኢትዮጵያ መንፈሳዊ ጉባኤ በሰኔ ፲፬ ቀን ፲፱፻፴፯ ዓ ም ተጽፈው ከነበሩት ጥያቄዎች ዓይነተኛውን ጉዳይ የሚቃወምና ሁለቱ ቤተ ክርስቲያኖች ወደ ስምምነት እንዳይደርሱ አድርጎ የሚከለክል ነው ።—

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪዋ የሚሆነውን ሊቀ ጳጳሳት በቋንቋዋ ከሚሰብኩላትና በመከራዋ ጊዜ ከማይለዩዋት ተወላጆችዋ ከሆኑ ከመንፈሳውያን አባቶች መካከል መርጣ እንድታቀርብና የእስክንድርያው ፓትሪያርክ ባርኮ እንዲሾምላት ፡ ሊቀ ጳጳሳቷም ሎሌቹን ጳጳሳት ከበታቹ ለመሾም መብት ያለው እንዲሆን ስትል ጠየቀች ። የኮፕት ጉባኤ ግን የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ለግብፃዊ ብቻ እንዲሆን ፈለገች ። ከቶውንም ይህ አሳብ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዘንድ እንደተወደደ አስመስሎ እውነት ነው የሚለው ሳይኖር አስታወቀች ።—

የተቀደሰው የኢትዮጵያ መንፈሳዊ ጉባኤ ሊቀበለው የማይሆንለት ከኮፕት ጉባኤ የመጣው ይህ ውሳኔ ለቤተ ክርስቲያን መሠረት የሆኑ ቅዱሳት መጻሕፍትንና የክርስትናን መንፈስ የሚቃወም መሆኑ በጉባኤው ተመርምሮ ታወቀ ። የክርስትና መንፈስ የወገንና የዘር ልዩነት አያደርግም ፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም አይሁዳዊ ፡ ወይም ዕርዕ ፤ ባርያ ፡ ወይም ነፃ የለም፡ ሁሉም በክርስቶስ አንድ ናቸው ብሎ ተናግሯል ።—

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በመልካም ትሕትና ያቀረበቻቸውን ዋነኞች ጥያቄዎች የኮፕት ጉባኤ ገፍታ መጣልዋን ከተረዱት በኋላ የጉባኤው አባሎች የሚከተለውን ውሳኔ አወጡ ።—

፩ኛ / በጠላት ወራሪነት ዘመን አቡነ ቄርሎስ ከጠላት ባለሥልጣናች ጋር ተስማምተው ብዙ ወራቶች ከቆዩ በኋላ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን በታች ናትና በጠቅላላው ያስተዳደሩ መብት እንዲሰጠኝ ሲሉ ያቀረቡት አሳብ እዚህ አዲስ አበባ ላይ የማይፈጸምላቸው ቢሆን ይህንኑ እስፈጽማለሁ ብለው ለጉባኤው ሳይገልጹ በሊቀ ጳጳስነቱ ሥራ አቡነ አብርሃምን ወክለው በፈቃዳቸው ወደኢጣልያ አገር ሔዱ ።—

በዚያም አሳባቸው የማይፈጸምላቸው ቢሆን ወደ ግብፅ ገብተው ስለቀሩ ቤተ ክርስቲያናችን ከመዘጋቱ በኋላ ይልቁንም ልዩ ልዩ የሆነ የባዕድ ሃይማኖት እየተስፋፋ የተዋሕዶ ሃይማኖት እየደከመ የሚሔድ ቢሆን በጊዜው ካሉት ባለሥልጣኖች አስፈቅደን ሃይማኖታችንን ለመጠበቅና የቤተ ክርስቲያናችንን ችግር ለማቃለል ስንል በተደነገገ በመንፈሳዊ ሥርዓት መክረን ሊቀ ጳጳሳትና ፡ ጳጳሳት ሾምን ።—

ይኸው አፈጻጸም ለሃይማኖታችንና ለቤተ ክርስቲያናችን መልካም አጠባበቅ ከመስጠት ጋር ምእመናኑን በሚገባ እያጽናና የጠላትን ዘመን በትዕግሥት እንዲያሳልፍ የተደረገ ነው እንጂ ከቅዱስ ማርቆስ አባትነት ለመለየት አይደለም ።ወደፊትም ቢሆን ቤተ ክርስቲያናችንን በመንፈሳዊ አስተዳደርዋ ራስዋን ችላ ከመኖርዋ በቀር በሃይማኖት ከቅዱስ ማርቆስ አባትነት የሚለያት የለም ።—

፪ኛ/የኮፕት ጉባኤ ከኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የቀረበላትን የትሕትና ጥያቄዎች በመቀበልና የሚገባትን ክብር በመስጠት ፈንታ እንደዚህ ያለ መልስ መጻፍ የሚያሳዝን ነው በዚህም አስተያየት ኮፕቶች የኢትዮጵያን ልጅነት እንዳልፈለጉ አረጋግጠዋል ሊባል የሚቻል ነው ።

እንግዲህ እንሱ አባት ለመሆን ሳይፈልጉ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የግብጽ ልጅ ልሁን እያለች ልትሽቆጠቆጥ የሚገባት አይደለም ።—

ወደፊትም የቅዱስ ማርቆስ አባትነት ሳይቀር ጳጳሳትንና ኤጲስ ቆጶሳትን ለመሾም ሥልጣን ያለው ኢትዮጵያዊ ሊቀ ጳጳሳት ከኢትዮጵያ መንፈሳዊያን አባቶች መካከል በሊቃውንት ሲኖዶስ ተመርጦ እንደ መጽሐፍ ሥርዓት ይሾማል እንጂ እንግዲህ ወደ ግብጽ የምንሔድበት ጉዳይ የለም ። በዚሁም ሁሉ ምክንያት ከዛሬ ጀምሮ ከግብፅ ኑኖት ጋራ የተለየን ሆነናል ። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ጉባኤ የወሰነው ይህ ውሳኔ ከንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ቀርቦ ፍጻሜ ያገኝ ዘንድ ጉባኤው ለብፁዕ ዕጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ያሳስባል ።—

በቤተ መንግሥቱ መልእክተኞችና በኢትዮጵያ መንፈሳዊ ጉባኤ መካከል

የተደረገ ንግግር ።

በኢትዮጵያ መንፈሳዊ ጉባኤና በእስክንድርያ ዐቢይ ጉባኤ መካከል ያለው የመስማማት አሳብ ወደ ፍጻሜንት ባለመድረሱ ምክንያት የኢትዮጵያ መንግሥት በበኩሉ በጉዳዩ ውስጥ ገብቶ ለማቅናት ፈቃዱ ስለሆነ፥ ከጉባኤው ተገኝተው ነገሩን የሚያጣሩ መልእክተኞች ቤተ መንግሥቱ ላከ ፣ በ፲፱፻፵፰ ዓ ም በኅዳር ፲፫ ቀን በተቀደሰው መንፈሳዊ ጉባኤ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መምህራን የሆኑ ሰባ ሁለት ሊቃውንትና ፳፬ መምህራን ስብሰባ አደረጉ ።—

በመጀመሪያ ጸሎት ማኅበር አድርሰው እግዚአብሔርን በሰቂለ ሕሊና ከለመኑ በኋላ ሁሉም በየማዕርጋቸው ተቀመጡ ። ከዚያም በኋላ ክቡር አፈ መስፍን እንዳርጋቸው መሳይ በቤተ መንግሥቱ በኩል ያለውን አስተያየት ካስረዱ በኋላ ፣ የጉባኤው አባሎች ነገሩን አጥንተው መልሱን እንዲሰጡ በማለት ለኅዳር ፲፯ ቀን ፲፱፻፵፰ ዓ ም ተቀጥሮ ጉባኤው ተመለሰ ።—

ኅዳር ፲፯ ቀን ሰኞ ከጧቱ በ፫ ሰዓት ተኩል ፫ኛው ፣ ስብሰባ ተደረገ፤ ሊቃውንቱም የተለመደውን ጸሎተ ማኅበር አድርሰው በየማዕርግ ሥፍራቸው ተቀመጡ ። በዚህም ጊዜ ከዚህ በታች የተጻፉት የቤተ መንግሥት መልእክተኞች በጉባኤው ውስጥ ነበሩ ።

ክቡር አፈ መስፍን እንዳርጋቸው መሳይ ፥
ክቡር ፊታውራሪ ታፈሰ ሀብተ ሚካኤል ፥
አቶ ዮፍታሔ ንጉሤ
ብላታ መርስዔ ኃዘን ወልደ ቂርቆስ ፥

በቤተ መንግሥት በኩል ስለዚህ ጉዳይ ያለውን አስተያየት ክቡር አፈ መስፍን እንዳርጋቸው በጉባኤው ፊት ቆመው አስታወቁ ።—

፻ የቤተ መንግሥት ሐሳብ ፥

ባለፈው ጉባኤ በቤተ መንግሥት በኩል ያለውን አስተያየት እኛ የቤተ መንግሥቱ መልእክተኞች ባጭሩ ገልጠንላችሁ ስለ ነበረ ፥ የናንተንም አስተያየት ተገንዝበንዋል ።

ይሁን እንጂ መንግሥት በበኩሉ ማድረግ የሚገባውን ጉዳይ ተነጋግሮ ገና አልጨረስም የምንል ነንና ፣ ከግርማዊነታቸው የተቀበልነውን ሐሳብ ዛሬ በሰፊው እንገልጽላችኋለን ።

ቤተ ክርስቲያን የቤተ ክህነትን ሰዎች እንደምትሰበስብ ፣ ቤተ መንግሥትም በምእመናን ሁሉ የተከበበ ነው ። በመጀመሪያው ጉባዔ በብፁዕ አባታችን አጨጌ ንግግር ውስጥ እንደሰማችሁት ቤተ ክርስቲያንና ቤተ መንግሥት የተባበሩ በመሆናቸው ነገሩ መልካም ፍጻሜ የሚያገኘው ሁለቱ ወገኖች ተገናኝተውና ተስማምተው በቆረጡት ነው ።—

ስለዚህ እስካሁን ድረስ ከእስክንድርያው ፓትሪያርክ ጋራ የተላላከችው ቤተ ክህነት ብቻ ናት ። የተገኘውም ፍሬ ነገር ደስ የሚያሰኝ አለመሆኑን ቤተ መንግሥታችን ስለተረዳው ፣ የቤተ ክህነት ሐሳብ ደጋፊ ሆኖ ቤተ ክህነት ያደረገችውን ትሕትና ያህል እሱም በወገኑ ከእስክንድርያው ጉባኤ ጋራ የሚገባውን ንግግር ማድረግ እንደሚገባው ተረድቶታል ።—

ይልቁንም ይኸንን የሚያህል ታላቅ ጉዳይ ሲቆረጥ ወደ እስክንድርያው ፓትረያርክ ፣ ወይም ወደጉባኤው አንድ ጊዜ እንኳ መላክተኛ ሳንልክና የቃል ንግግር ሳናደርግ በወረቀት መልክት ብቻ ይህን ያህል ዘመን በፈቃዳችን የያዝነውን ነገር ልንተወው አይገባንም ።—

ቤተ ክህነታችን እስካሁን ድረስ ስትለምን ቆይታ ከወገንዋ ሊቀ ጳጳሳትዋን ለመምረጥና ለመሾም አትችልም የሚል ምላሽ ከመጣላት ወዲህ ከኮፕት ጉባኤ ጋራ ግንኙነቷን ለመተው ማሰቧ የሚታሰብበት ነገር መሆኑን መንግሥት የሚገነዘበው ነው ።— የንጉሠ ነገሥቱም መንግሥት በተራው እንደዚሁ መልእክተኛውን ልኮ ቤተ ክህነት በጠየቀችው መሠረት ከእስክንድርያው ፓትሪያርክ ጋራ ከተነጋገረ በኋላ በኅብረት የቀረበላቸውን ጥያቄና ልመና እንደገና ገፍተውት የሚገኙ የሆነ እንደሆነ ጉዳዩ መፈጸሚያ ያገኛል ።—

ክቡር አፈ መስፍን አንዳርጋቸው መሳይ ከዚህ ከተጻፈው በቀር ልዩ ልዩ ማስረጃ እያመጡ በሰፊው ተናግረው ካስረዱ በኋላ ፣ ክቡር ፊታውራሪ ታፈሰ ሀብተ ሚካኤል ይህን ሐሳብ በመደገፍ ለጉባኤው ሲያስረዱ የሚከተለውን አስታወቁ ።—

በምስር ሳለሁ፣ እንደተመለከትሁት መጠን ከግብፃውያንም ምሁራንና መንፈሳውያን የሆኑት አባቶች የሚገባንን መብት በመንሳት ሁለቱን ቤተ ክርስቲያኖች አለያይቶ ማስቀረት ደስ የሚያሰኛቸው አይመስልም ። ቤተ ክርስቲያናችን ያቀረበቻቸው ጥያቄዎች በሕጋኛው መንገድ ላይ የቆሙ ናቸውና ምን ጊዜም ቢሆን ወዳሰብነው ሐሳብ ለመድረስ ከልካይ የለብንም ። ይሁን እንጂ የመንግሥታችን ትሕትና ባለዋጋ ፈንዲሆን መልእክተኞቹ አሁን በመጀመሪያው ሄደው አስፈላጊውን ጥያቄ እንዲያቀርቡና ምላሹን ሲያስታውቁ ሐሳባችንን ብንቀጥል የተሻለ ይሆናል ።—

የሊቃውንቱ ንግግር ።

ሊቃውንቱ ስለማስረጃ ከቅዱሳት መጻሕፍት ልዩ ልዩ ቃል እየጠቀሱ በየተራ ሐሳባቸውን ከገለጹ በኋላ፣ የዛጉባሬት ውሳኔያቸውን አስታወቁ ። ይኸውም ውሳኔ ቀጥሎ የተፈጸው ነው ።—

## የኢትዮጵያ ዐቢይ መንፈሳዊ ጉባኤ የሰጠው ውሳኔና

## የእጨጌው ማሳሰቢያ ።

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን ።

ብፁዕ እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ የጉባኤው ሰብሳቢ ሆነው በተቀመጡበት በዚህ ውሳኔ መጨረሻ ስማቸውን የፈረሙ ፸፪ ሊቃውንትና ፳፬ መምህራን ፣ ከነርሱም ፲፯ቱ የቆሞስነት ማዕርግ ያላቸው መምህራንና ሊቃውንት ።—

በ፲፱፻፴፰ ዓ ም በኅዳር ፱ ቀን እሑድ ፣ ዳግመኛ በኅዳር ፲፫ ሐሙስ ፣ ሦስተኛም በኅዳር ፲፯ ቀን ሰኞ አዲስ አበባ በቅድስት ሥላሴ ጉዳም ተሰብስበው ወደ እግዚአብሔር ጸሎት አድርገው ከተነጋገሩ በኋላ የሚከተለውን ውሳኔ አወጡ ።—

፩ኛ / ጉባኤው የተሰበሰበበት የነገሩ ዋነኛው አርእስት ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳሳት መሆን የሚገባው ኢትዮጵያዊ ወይስ ግብፃዊ እንደሆነ ለመለየትና መንፈሳዊ ውሳኔን ለመስጠት ነው ። በዚህ ጉዳይ ምክንያት በየጊዜው የተጻፉትን ነገሮች ጉባኤው መረመረ ።—

ሀ / ይልቁንም የኢትዮጵያ መንፈሳዊ ጉባኤ በሰኔ ፳፮ ቀን ፲፱፻፴፯ ዓ ም ከ፯ ጥያቄ ዎች ጋራ የጻፈውንና ለእስክንድርያ ፓትረያርክ የላከውን ደብዳቤ ።—

ለ / የእስክንድርያ ፓትረያርክ አንድ ዓመት ያህል ቆይተው የኢትዮጵያ መንፈሳዊ ጉባኤ ካቀረባቸው ጥያቄዎች አይነተኞቹን ሁለቱን ጉዳዮች አለመቀበላቸውን እያስረዱ ፣ ትእዛዝ ብለው በ፲፱፻፴፯ ዓ ም ሰኔ ፱ ቀን የጻፉትንና ለኢትዮጵያ መንፈሳዊ ጉባዔ የላኩትን ቃል ።—

ሐ / የኢትዮጵያ መንፈሳዊ ጉባኤ በ፲፱፻፴፯ ዓ ምሐምሌ ፯ ቀን ለኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ያቀረበውን የውሳኔ ማስታወቂያ ።—

፪ኛ / ጉባኤው ከመረመራቸው ነገሮች አንዳንዶቹን ከዚህ ማንሣት አስፈላጊ ነው፤
ሀ/ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የጠየቀችው ሊቀጳጳሳትዋ ከተወላጆችዋ መካከል በሊቃውንቶችዋ እየተመረ ጠ የእስክንድርያ ፓትረያርክ ባርከው እንዲሾሙላት፤ ሊቀ ጳጳሳትዋም በበታቹ ጳጳሳትንና አዲስ ቆጶሳትን ለመሾም መብት ያለው እንዲሆን ነው፤

፩ኛ / የኮፕት ቤተ ክርስቲያን ግን ፤ በኢትዮጵያ የሚሾመው ሊቀ ጳጳሳት ለዘለዓለም የግብፅ ሰው ብቻ እንዲሆን እንጂ ኢትዮጵያዊ አይሆንም ስትል መልስ ሰጠች። ለዚህም ማስረጃ ሺህ ስድስት መቶ ዘመን የቆየ ልማድ መሆኑን ከማስታወስ በላይ ከቅዱሳን አበው ከሠለስቱ ምዕት በጉባኤ ኒቅያ ተጽፎ የተወሰነ ነው ስትል አሳብዋን አስታወቀች ።—

## የጉባኤው ምርመራ ፤

የተቀደሰው ዐቢይ መንፈሳዊ ጉባኤ ከጭብጣውያን በኩል የቀረቡትን አሳቦች ከመረመረ በኋላ የሚከተሉትን ነገሮች እነሆ ያስታውቃል ።—

/ሀ/ ስለዘመን ብዛት ።

የዘመን ብዛት ልማድን ፤ ወይም ሥርዓትን ከማሻሻል የሚያግድ አይደለም ። ብዙ ዘመን የኖረው የአሪት ሥርዐት እንዳይሻሻል የዘመኑ ብዛት አላገደውም ። እንዲሁ ደግሞ በልዩ ልዩ አምልኮት የሚኖሩ አረማውያን አሁን በወንጌል ሲያምኑ የዘመኑ ብዛት ሥርዓት ሆኖ አያግዳቸውም ፡ ይህን የመሰለ ብዙ ምሳሌ ይገኛልና ነገሩን ባጭሩ መተው አስፈላጊ ነው ።—

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በፈቃድዋ ትሠራበት የነበረውን ልማድ አሁን ደግሞ በፈቃድዋ ታሻሽለው ዘንድ የሚገባት ሆነ ። ምክንያቱም የቀድሞው ልማድ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ላይ ብርቱ ጉዳት የሚያደርስባት መሆኑ በሚከተሉት ምክንያቶች ስለተገለጸ ነው ።—

በኢትዮጵያ ላይ የሚሾሙት ግብፃውያን ሊቃነ ጳጳሳት ።

፩ኛ / የሕዝቡን ቋንቋ የሚያውቁና በሕዝቡ ቋንቋ የማይሰብኩ ናቸው ።

፪ኛ / በቤተ ክርስቲያናቱ ወይም በአገሩ አደጋ በደረሰ ጊዜ ወዳገራቸው የሚሄዱ ናቸው፤ ከዚህም በቀር ለጠቅላላው አስተዳደር እንቅፋት የሚሆን ምክንያትን የሚያስከትል መሆኑ አይጠረጠርም ።—

ይህንን ሁሉ በማመዛዘን ፡ የቆየው ልምድ በሚገባ እንዲለወጥ አስፈለገ ።

/ለ/ ስለ ኒቅያ ጥቅስ ።

የኮፕት ቤተ ክርስቲያን የግል ጥቅምን ለመመሥረት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዘላለም በበታችዋ ሆና እንድትኖር ለማድረግ ምክንያት ሆኖ በየጊዜው የሚጠቀሰውን ቃል ጉባኤው መረመረ ፡ ቃሉም « የኢትዮጵያ ሰዎች ከአዋቂዎቻቸው ወገን ሊቀ (ሊቀ ጳጳሳት) አይሹሙ የሚለው ነው ይህ ጥቅስ በኢትዮጵያ ውስጥ አዋቆች መኖራቸውን እየመሰከረ ሹመቱን ብቻ ይከለክላል ። ይኸውም ቃል ለጥቅም ሲባል የተፈጠረ መሆኑን የሚከተሉት ምክንያቶች ያስረዳሉ ።—

ሀ / ይህ ቃል በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ስለማይገኝ ፡

ለ / የክርስትና ሥርዓት የዘርና የወገን ልዩነት ስለሚያደርግ ፡

ሐ / ኢትዮጵያ ሥርዓት ክርስትናን የተቀበለችው ከኒቅያ ጉባኤ በኋላ ስለሆነ ከማመንዋ በፊት የኒቅያ ጉባኤ ይህን ዓይነት ውሳኔ እንደማያወጣባት ለባለ አእምሮው ሁሉ የተገለጠ ስለሆነ ነው ።—

በዚህና ይህን በመሰለ ምክንያት ሁሉ ከግብፃውያን የተጠቀሰው ጥቅስ ቀዋሚነት ያለው ሆኖ አልተገመተም ፡ ከዚህም በቀር ጉባኤው የተመለከተው ነገር አለ ፡ከግብፃውያን የተጠቀሰው ይህ ቃል እውነት ነው ቢባል ኖሮ እንኳን ፡ የአስተዳደር ጉዳይ ነው እንጂ ፤ የሃይማኖት ነገር አይደለም ። የአስተዳደር ነገር ለዘመኑ የሚስማማው በየጊዜው እየታየ ይሻሻል ዘንድ የሚገባ ስለሆነ እንዲሻሻል ፡ ወይም እንዲለወጥ ከማድረግ የሚከለክል አንዳች ምክንያት አለመኖሩ የታወቀ ነው ።—

/ሀ/ ስለዘመን ብዛት ።

የዘመን ብዛት ልማድን ፤ ወይም ሥርዓትን ከማሻሻል የሚያግድ አይደለም ። ብዙ ዘመን የኖረው የአሪት ሥርዐት እንዳይሻሻል የዘመኑ ብዛት አላገደውም ። እንዲሁ ደግሞ በልዩ ልዩ አምልኮት የሚኖሩ አረማውያን አሁን በወንጌል ሲያምኑ የዘመኑ ብዛት ሥርዓት ሆኖ አያግዳቸውም ፥ ይህን የመሰለ ብዙ ምሳሌ ይገኛልና ነገሩን ባጭሩ መተው አስፈላጊ ነው ።—

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በፈቃድዋ ትሠራበት የነበረውን ልማድ አሁን ደግሞ በፈቃድዋ ታሻሽለው ዘንድ የሚገባት ሆነ ። ምክንያቱም የቀድሞው ልማድ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ላይ ብርቱ ጉዳት የሚያደርስባት መሆኑ በሚከተሉት ምክንያቶች ስለተገለጸ ነው ።—

በኢትዮጵያ ላይ የሚሾሙት ግብፃውያን ሊቃነ ጳጳሳት ።

፩ኛ / የሕዝቡን ቋንቋ የሚያውቁና በሕዝቡ ቋንቋ የማይሰብኩ ናቸው ።

፪ኛ / በቤተ ክርስቲያናቱ ወይም በአገሩ አደጋ በደረሰ ጊዜ ወዳገራቸው የሚሄዱ ናቸው፤ ከዚህም በቀር ለጠቅላላው አስተዳደር እንቅፋት የሚሆን ምክንያትን የሚያስከትል መሆኑ አይጠረጠርም ።—

ይህንን ሁሉ በማመዛዘን ፥ የቆየው ልምድ በሚገባ እንዲለወጥ አስፈለገ ።

/ለ/ ስለ ኒቅያ ጥቅስ ።

የኮፕት ቤተ ክርስቲያን የግል ጥቅምን ለመመሥረት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዘላለም በበታችዋ ሆና እንድትኖር ለማድረግ ምክንያት ሆኖ በየጊዜው የሚጠቀሰውን ቃል ጉባኤው መረመረ ፥ ቃሉም « የኢትዮጵያ ሰዎች ከአዋቂዎቻቸው ወገን ሊሊቃ (ሊቀ ጳጳሳት) አይሹሙ» የሚለው ነው ይህ ጥቅስ በኢትዮጵያ ውስጥ አዋቆች መኖራቸውን እየመሰከረ ሹመቱን ብቻ ይከለክላል ። ይኸውም ቃል ለጥቅም ሲባል የተፈጠረ መሆኑን የሚከተሉት ምክንያቶች ያስረዳሉ ።—

ሀ / ይህ ቃል በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ስለማይገኝ ፥

ለ / የክርስትና ሥርዓት የዘርና የወገን ልዩነት ስለሚያደርግ ፥

ሐ / ኢትዮጵያ ሥርዓት ክርስትናን የተቀበለችው ከኒቅያ ጉባኤ በኋላ ስለሆነ ከማመንዋ በፊት የኒቅያ ጉባኤ ይህን ዓይነት ውሳኔ እንደማያወጣባት ለባለ አእምሮው ሁሉ የተገለጠ ስለሆነ ነው ።—

በዚህና ይህን በመሰለ ምክንያት ሁሉ ከግብፃውያን የተጠቀሰው ጥቅስ ቀዋሚነት ያለው ሆኖ አልተገመተም ፥ ከዚህም በቀር ጉባኤው የተመለከተው ነገር አለ ፥ ከግብፃውያን የተጠቀሰው ይህ ቃል እውነት ነው ቢባል ኖሮ እንኳን ፥ የአስተዳደር ጉዳይ ነው እንጂ ፤ የሃይማኖት ነገር አይደለም ። የአስተዳደር ነገር ለዘመኑ የሚስማማው በየጊዜው እየታየ ይሻሻል ዘንድ የሚገባ ስለሆነ እንዲሻሻል ፥ ወይም እንዲለወጥ ከማድረግ የሚከለክል አንዳች ምክንያት አለመኖሩ የታወቀ ነው ።—

ቃላቸውም እንደሚከተለው ነው ።—

፩ኛ/ በኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳትም ፥ ጳጳስም የሚሾመው ከኢትዮጵያ መምህራንና መነኮሳት ውስጥ ብቻ እንዲሆን ብሎ መንፈሳዊ ጉባኤ ፲፱፻፵፯ ዓ ም በሰኔ ፳፩ ያቀረበው ዋና ጥያቄ የሚገባ መሆኑን ተስማምቶበታል ።—

፪ኛ/ የእስክንድርያው ፓትረያርክ ይህን ጥያቄ ያልተቀበሉት በማይበቃ ምክንያት መሆኑን መላው ጉባኤ ተረድቶታል ።—

፫ኛ/ መላው ጉባኤ ለኢትዮጵያ የሚገቡት ሊቀ ጳጳሳትና ጳጳሳት ከኢትዮጵያ ተወላጆች ውስጥ እንዲመረጡ ማስፈለጉን ተስማምቶበታል ። ይኸውም አሳብ በመንግሥታችን ወገን የተደገፈ ስለሆነ ፥ መንግሥታችን መልእክተኞቹን ልኮ አሳቡን ለመፈጸም የሚከናወንለት ከሆነ ጉባኤው ተቃዋሚ አይደለም ፥

ስለዚህ ፥ የቤተ መንግሥታችን አሳብና ምኞት መልእክተኞቹን ልኮ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የጠየቀችውን ሁሉ ከእስክንድርያው ፓትረያርክ ተጠባባቂ ፤ ወይም ከጉባኤው ጋራ በሰላም ለመጨረስ ስለሆነ ይኸንኑ በቶሎ ከፍጻሜ እንዲያደርሱላት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ግርማዊነትዎን በጸሎት እየደገፈች ትለምናለች ።—

ነገር ግን ፤ ግርማዊነትዎ መልእክተኞቹን ልኮ ካሁን በፊት በዚሁ ነገር ቤተ ክህነት የደከመችውን ያህል በኑሩ ደክመውበት ከእስክንድርያ ፓትረያርክ ተጠባባቂ ወይም ከጉባኤው ፍሬ ያለው ምላሽ ያልተገኘ እንደሆነ ፥ አሁን ዐቢይ ጉባኤያችን በቀረጠው ነገር ግርማዊነትዎ የተስማማ እንዲሆን ባለመጠራጠር እናምናለን ።—

ኅዳር ፳፱ ቀን ፲፱፻፵፰ ዓ ም አዲስ አበባ

እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት

የመልእክተኞች መላክና በሁለቱ ቤተ ክርስቲያኖች መካከል ንግግር ስለመደረጉ ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ጉባኤ በኅዳር ፱ ፤ ፲፫ና ፲፯ ቀን ፲፱፻፵፰ ዓ ም የመከረበትንና የወሰነውን ነገር መሠረት በማድረግ ከእስክንድርያ ፓትረያርክ ጋር እንዲነጋገሩና ጉዳዩን በስምምነት እንዲጨርሱ የመንግሥት መልእክተኞች ፊታውራሪ ታፈሰ ሀብተ ሚካኤልና ብላታ መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ ወደ ካይሮ ተላኩ ። መልእክተኞቹም ከጥር ፲፯ እስከ መጋቢት ፲፪ ቀን ድረስ ከተጠባባቂው ፓትረያርክና ከአቡነ አትናቴዎስ ጋር በመነጋገርና በመከራከር ፶፭ ቀኖች አሳለፉ ። የመልእክተኞቹ ጥያቄ ኢትዮጵያውያን ጳጳስና እንዲሾሙ ፤ ከእነርሱም መካከል አንዱ ሊቀ ጳጳሳት እንዲሆንና በውስጡ ጳጳሳትን ለመሾም መብት ያለው እንዲሆን የሚል ነበር ። ፓትረያርኩ አቡነ መቃርዮስ ካረፉ ጀምሮ ፓትረያርኩ ገና ስላልተሾሙ በተጠባባቂ ይተዳደር ነበር ። ተጠባባቂውም ፓትረያርክ ነገሩን በስምምነት ለመፈጸም የሚስማሙ መሆናቸውን ገለጹ ። ይሁን እንጂ ማናቸውም ነገር ፍጻሜ ሊያገኝ የሚችለው ፓትረያርኩ ከተሾመ በኋላ በመሆኑ፥ በግንቦት ፪ ቀን ፲፱፻፵፰ ዓ ም የሚደረገው የፓትረያርክ ምርጫ የኢትዮጵያ መልእክተኞችና የሚቀበሉት መነኮሳት ካይሮ ላይ እንዲ

ገኙ ተብሎ ተወሰነ ። የኢትዮጵያ መልእክተኞች ይህን ውሳኔ ተቀብለው መጋቢት ፲፪ ቀን ፲፱፻፵፰ ዓ ም ከካይሮ ተመልሰው አዲስ አበባ ገቡ ። ሚያዝያ ፳፰ ቀን ፲፱፻፵፰ ዓ ም ሁለቱ መልእክተኞችና ለጵጵስና የተመረጡት ፭ቱ አባቶች በኢትዮጵያ የየር መንገድ ከአዲስ አበባ ተነስተው ዕለቱን ካይሮ ደረሱ ። ግንቦት ፪ ቀን የፓትረያርኩ ምርጫ ሲደረግ ኢትዮጵያውያኑም የምርጫው ተካፋይ ሆነው ቀረቡና መረጡ ። የምርጫው ዕጣ ለገርጋ መጥራን ለአቡነ ዮሳብ ስለወጣ ግንቦት ፲፰ ቀን እሑድ ዮሳብ ዳግማዊ የ፲፭ኛ ፓትረያርክ ተብለው በመንበረ ማርቆስ ተቀመጡ ። በግንቦት ፳፬ ቀን የኢትዮጵያ መልእክተኞች ጉዳያቸውን አቅርበው ንግግር ጀመሩ ። በጉዳዩ ማጅሊስ ሚሊ የሚባለው የሕዝብ ጉባኤ ስለገባበት ጉዳዩን ለማቃናት አስቸጋሪ ሆኖ ነበር ። ዋናውም ክርክር የኢትዮጵያው ሊቀ ጳጳሳት በውስጡ ጳጳስ ይሾም ዘንድ መብት አይ ስጠውም በማለታቸው ነበር ። የኢትዮጵያ መልእክተኞች ነገሩን በሰላም ለመፈጸም ይደክሙበት ስለነበር ፥ ጳጳሳትን የመሾም ነገር የሚያከራክር ከሆነ ለወደፊት ንግግር ይደረግባታል ይቆይ ፥ አሁን ለመነኩሳቱ ሢመተ ጵጵስናው ይደረግላቸው የሚል መስሚያ ኢሳብ አድርገው ነበር ፥ ዳሩ ግን ይህን አሳብ ስላልተቀበሉት መነኩሳቱ ወደ አዲስ አበባ ለመመለስ ቆርጠው ነበርና ፥ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቴሌ ግራም ለብፁዕ ፓትረያርኩ አሳለፉላቸው ።—

የግርማዊነታቸው ቴሌግራም

ለቅዱስ አባ ዮሳብ ፥

ቅዱስነትዎ የላኩልን ቴሌግራም ደረሰን ፥ ለሹመት የቀረቡት ጳጳሳት በበኩላቸው ያሳለፉልን ቃል ፥ አንደኛ የኢትዮጵያ መንፈሳዊ ጉባኤ ለተስማማበት ጉዳይ የተላክን ስለሆን ጉባኤው አንቀበለውም ያለውን ነገር ተቀብላችሁ ፈርሙ ቢሉን ባልተላክን በት ጉዳይ አንፈርምም በማለት ፥

፩ኛ / በቀረበው ሁሉ ተስማምተን ያልተስማማንበት ጉዳይ የሠለስቱ ምዕት ሲኖዶስ ለኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ የሚያዝለትን ፈቃድ አንሠራም ብላችሁ ፈርሙ ስለተባልን ይህ ፈቃድ ተጽፎ የኖረ ትእዛዝ ነው እንጂ የኢትዮጵያ መንፈሳዊ ጉባኤ አዲስ የፈ ጠረው ነገር አይደለምና አንቀበለውም በማለት ለመስማማት አልቻልንም ።—

፪ኛ / ይህንኑም አሳባችንን የዛሬው የግብፅ ሲኖዶስ የማይቀበለው ከሆነ ኤጲስ ቆጳሳትን የመሾማችን ጉዳይ በሬዜርብ ቆይቶ በኋላ ይመከርበት ፥ በዋናዎቹ ጉዳዮች ግን ከማርቆስ መንበር አባትነትና ሊቀ ጳጳሳት እንዳንሾም እንፈርም ብለን ተቀብለ ናል የሚል ነው ። ለመሾም የቀረቡት ጳጳሳት ባልተስማሙበት ጉዳይ ተገድደው እን ዲፈርሙ ቅዱስነትዎ እንዲጠየቀን የእኛ ትእዛዝ እንዲያልፍላቸው ለማድረግ በሕግ አስተያየት በኩል ማስገደዱ ሕግን የሚጥስ ነገር ሆኖብን ፥

የተላኩት ጳጳሳት የሚያከራክረውን የኤጲስ ቆጳስ መሾም ነገር ዛሬውኑ ይፈቀድ ልን ሳይሉ በሬዘርብ ቆይቶ የሹመቱ ጉዳይ ይለቀልን ማለታቸው በፍቅር መኖርን እንጂ መለያየትን አለመፈለጋቸውን የሚያሳይ አኳኋን ነው ። የሃይማኖት መለያየት ሳይኖርብን ባጀጀም ብቻ ሳይስማሙ ቀርተው ፥ ለዚያውም የኢትዮጵያ ወገኖች ያቀረ

ቡትን ሬዜርብ ሳይቀበሉዋቸው ቀርተው ተለያዩ መባል ለግብፅ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ክፉ ስም እንዳይሰጥ ይህን የሚአከራክረውን የሺማኒት የሥጋዊ ክብር ጉዳይ ቅዱስ ነትዎ በሬዜርብ እንዲቀይ አድርጎ የተስማማችሁበት ጉዳይ ተፈርሞ ጳጳሳቶቹ ተሾመው እንዲመጡ በማድረግ መለያየትን እንዲያስቀሩ እንለምንዎታለን ።

የኢትዮጵያ መንፈሳዊ ጉባኤ ጠላት ወደ ኢትዮጵያ በገባ ጊዜ አቡነ ቄርሎስ ትተውት በመሔዳቸው ምክንያት ተስፋ ቆርጦ መለያየቱን ግልጽ ሆኖ መቸም ሰምቶ ከቆየ በኋላ ፣ ወደ እዚህ ወደ አዲሱ መቀራረብ የመለስነው በብዙ ጥረት ስለሆነ ይህን በብርቱ የደከምንበትንና በእግዚአብሔር ቸርነት የተቃረበውን ስምምነት ጳጳሳቶቹ ሳይሾሙ በመመለሳቸው እንዳያፈርሰው በሃይማኖት አምላክ ስም ለቅዱስነትዎ አደራ እንላለን ። ሰኔ ፲፩ ቀን ፲፱፻፴፰ ዓ ም

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ
የፓትርያርኩ ቴሌግራም ።

ለግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ
አዲስ አበባ ።

የግርማዊነትዎንና የኢትዮጵያን የልጆቻችንን ምኞት ለመፈጸም ውዲቱን የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያንም ሥራዋን እንድትፈጽም እሑድ ሰኔ ፱ ቀን ፴፰ ዓ ም አምስቱን ኢትዮጵያውያን ለመቅባት እንደቀረጥንና እነዚሁ እንዲቀቡ የተመደቡት ጥንት ጀምሮ ሲደረግ የነበረውን ሥርዓት ትራዲሽናል / ግዴታውን ለማስታወቅ እንዲፈርሙ ቢጠየቁ እምቢ በማለታቸው በጣም ገረመን፤ ይኸውም በሚቼ / ቅዱስ / አባ ዮሐንስ ጊዜ አምስቱ ሲቀቡ የተደረገውንና ተከብሮ የቆየ ሥርዓት ነው ፣ ግርማዊነትዎ ስለ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ያላዎትን ታላቅ ታማኝነት እያሳሰብሁ ፣ የሁለቱ ቤተ ክርስቲያኖች ታሪካዊ መገናኛ እንዲጠበቅ ለተፈጠረው ግጭት ከፍ ያለው የግርማዊነትዎ አስተዋይነት መድኃኒት (ዘዴ) እንዲ አገኝለት እየተማመንሁ የቅብዓቱ ሥርዓት በተቆረጠው ቀን እንዲፈጸም መልእክተኞቹ ግዴታቸውን እንዲፈርሙ የምክር ቃል እንደተቻለ በቶሎ እንዲአልፍላቸው ግርማዊነትዎን እለምናለሁ ።—

ይኸውም በውዝፍ የቆየውን ጉዳይ ለማከናወን የሚፈቅድልን ይሆናል ፣ ለግርማዊነትዎና ለቤተ መንግሥቱ ቤተ ሰቦች ቡራኬዬን አቀርባለሁ ። ሰኔ ፰ ቀን ፲፱፻፴፰ ዓ ም

ዮሳብ ሁለተኛ ጳጳስና ፓትሪያርክ ።

ብፁዕ ፓትሪያርክ ይህን መልእክት ከተቀበሉ በኋላ ዶክተር ኢብራሂም ሚኒብ ፖሻና ቆሞስ ኢብራሂም ሉቃስ አዲስ አበባ እንዲነጋገሩ አዘዙዋቸው ። መልእክተኞቹ በሐምሌ ፲፫ አዲስ አበባ ገቡ ፤ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በኩል ነገሩን በኀላፊነት የሚመረምር የመኳንንት ጉባኤ ተቋቋመና ፱ ቀን ያህል ንግግር ተደረገ ። ነገር ግን ዋናው መልእክተኛ ዶክተር ሚኒያቢፖሻ ወደ ስምምነት የማይቀርቡ ስለሆነ ሐምሌ ፳፯ ፤ ፴፰ ዓ ም ወደካይሮ ተመለሱ ።—

ከዚህ በኋላ ለድርድሩ ቀብዓት በካይሮ ላይ የነበሩት የኢትዮጵያ ጳጳሳት ወደ አዲስ አበባ እንዲመለሱ ተደርጎ ሐምሌ ፳፱፣ ፴፰ ዓ ም አዲስ አበባ ገቡ ። ከዚህ በኋላ የስምምነቱ ነገር እንዲቀጥል ከሁለቱ ወገን ስለተፈቀደ የሁለቱን ቤተ ክርስቲያኖች መተባበር በሚወድ በኑቴውልክፋዚ ፖሻና በነሳብ ሐበሽ ፖሳ አማካይነት አንዳንድ ጊዜም በቀጥታ የስምምነቱ ንግግር አልተቋረጠም ።

<u>በሁለቱ ቤተ ክርስቲያናት መካከል ስምምነት ስለመገኘቱ ፤</u>

በግብፅና በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መካከል የተደረገው ንግግር ወደመልካም ፍጻሜ ባለመድረሱ ምክንያት ብዙ ዘመን ጸንቶ የቆየውን የሁለቱን ቤተ ክርስቲያኖች ግንኙነት እንዳይራራቅና ከግብፃውያን ወንድሞቻችን ጋር ያለው ወዳጅነት እንዳይበርድ የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት በጉዳዩ ውስጥ ገብቶ ነገሩን ወደስምምነት እንዲመራው ስለታሰበ በኢትዮጵያ መንፈሳዊ ጉባኤ በኩል ያለው የጋለ ስሜት ወደ ትዕግሥት እንዲመለስ ፤ የቤተ መንግሥት መልእክተኞች ለጉባኤው ምክራቸውን አካፈሉ ። ከዚህም በኋላ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ካይሮ በሚገኘው ሌጋሲዮናቸው በኩል ንግግር ጀመሩ ። በዚህም ሁኔታ ከእስክንድርያው ፓትሪያርክ ጋር በመነጋገር ብዙ ጊዜ ቆይተው ከ፩ ዓመት ድካም በኋላ እግዚአብሔር በፈቀደበት ጊዜ ሐምሌ ፯ ቀን ፲፱፻፵ ዓ ም ነገሩ ወደ ስምምነት ደረሰ ።

የስምምነቱ የመጨረሻ አሳብ እንደታወቀ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በአሉበት ሐምሌ ፲፫ ቀን ፲፱፻፵ ዓ ም ታላቅ ጉባኤ ተደረገ ። በጉባኤውም ስማቸው ከዚህ ቀጥሎ የሚገኘው ልዑላን መሳፍንትና ክቡራን ሚኒስትሮች ፤ ሊቃውንትና ታላላቅ መኳንንት ነበሩ ።—

ልዑል መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ፤ ልዑል መኰንን መስፍነ ሐረር ፤ ብፁዕ እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ፤ አሁን / ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ፤ ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ ፤ ልዑል ራስ ካሣ የዘውድ አማካሪ ፤ ክቡር ራስ አበበ አረጋይ የዘውድ አማካሪና የጦርሚኒስትር፤ ክቡር ራስ ቢትወደድ መኰንን የዘውድ አማካሪና ጠቅላይ ሚኒስትር ፤ ክቡር ራስ ኃይሉ በለው የዘውድ አማካሪ ፤ ክቡር ደጃዝማች ታዬ፤ ጉልላቴ ክቡር ፤ ብሪጋድየር ዤኔራል ዐቢይ አበበ፤የጦር ምክትል ሚኒስትር፤ክቡር ጸሐፌ ትእዛዝ ወልደ ጊዮርጊስ የጽሕፈትና ያገር ግዛት ሚኒስትር ፤ ክቡር አቶ መኰንን ሀብተ ወልድ የንግድና የእንዱስትሪ ሚኒስትር ፤ ክቡር ጸሐፌ ትእዛዝ ኃይሌ ወልደ ሩፌ ፤ የዘውድ አማካሪ ፤ ቢትወደድ ነጋሽ በዛብህ በጠቅላይ ሚኒስቴር የአማካሪ ሚኒስትር ፤ ክቡር አፈ ንጉሥ ዘውዴ አየለ፤ ደጃዝማች መንገሻ ውቤ የሕግ መወሰኛ ምክ ቤት ፕሬዚዳን ፤ አቶ መኰንን ደስታ የሕግ መምሪያ ምክር ቤት ፕሬዚዳን፤ ክቡር አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ የውጭ ጉዳይ ምክትል ሚኒስትር ፤ ክቡር አቶ ይልማ ዴሬሳ የገንዘብ ምክትል ሚኒስትር ፤ ብላታ ዘውዴ በላይነህ የሥራና የመገናኛ ምክትል ሚኒስትር ፤ ደጃዝማች በዛብህ ስለሺ በአገር ግዛት ምክትል ሚኒስትር ፤ ክቡር አቶ አበበ ረታ የሕዝብ ጤና ጥበቃ ምክትል ሚኒስትር ፤ ክቡር አቶ አርአያ አበበ በጠቅላይ ሚኒስቴር የሕግ አፈጻጸም ምክትል ሚኒስትር ክቡር ብላታ ዴሬሳ አመንቴ በጠቅላይ ሚኒ-

ስቴር የአድሚኒስትራሲዮን ፍርድ ቤት ምክትል ሚኒስትር ፡ ክቡር ሊቀ ሥልጣናት መልአክቱ /አሁን/ ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ ፤ ብላታ መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ ፡ ፀባቴ ጥዑመ ልሣን ፡ መምህር ሐረገ ወይን ፤ መምህር ወልደ ሥላሴ ፤ መልአከ ፀሐይ ዘለቀ ፡ መልአከ ገነት ሀብተ ወልድ ፡ መምህር ወልደ ጊዮርጊስ ፡ መልአከ ኃይል ኃይለ ሥላሴ መልአከ ኃይል ተድላ ፡ መምህር ራስ ወርቅ ፡ አለቃ መኰንን አለቃ ማርቆስ ፡ ሊቀ ጠበብት ውቤ ፡ መምህር ተክለ ጊዮርጊስ ፡ ልዑላን መሳፍንትና ክቡራን መኳንንት የየማዕርግ ሥፍራቸውን ከያዙ በኋላ የጽሕፈትና ያገር ግዛት ሚኒስትር ክቡር ጸሐፌ ትእዛዝ ወልደ ጊዮርጊስ ጉባኤው የተሰበሰበበትን ምክንያት የሚገልጠውን የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቃል አነበቡ ።—

የተነበበውም ቃል የሚገልጠው አሳብ ከዚህ በታች የተመለከተው ነው ።

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንና በግብፅ ኮፕት ቤተ ክርስቲያን መካከል ስለኢትዮጵያ ውያን ጳጳሳት መቀባት ተነሥቶ የነበረውን የአሳብ ልዩነት ሁላችሁም የምታውቁት ነው ። እኛም መልእክተኞች ልከን ፓትሪያርኩም በመጨረሻው መልእክተኞቹን አዲስ አበባ ድረስ እንዲልኩ ተደርጎ ፡ እየተደጋገመ ብርቱ ንግግር ከሆነ በኋላ ፡ ለመስማማት ሳይቻል ስለቀረ ፡ ነገሩ ሳይጨረስ በቆየበት ጊዜ ሁሉ ከፓትሪያርካው ጋር በመልእክትም በደብዳቤም ነገሩ ወደመልካም ፍጻሜ እንዲደርስ መድከማችን አልቀረም ነበር ።—

አሁንም በመጨረሻው በግብፅ የሾምነው ሚኒስትራችን ፊታውራሪ ታፈሰ ወደሥራው ሲሔድ እንደገና ነገሩ ሊጨረስ የሚገባበትን መንገድ አስጠንተን ትእዛዛችንን በጽሕፈት ይዞ ሔዶ ነበርና ከእርሱም ከፓትሪያርካውም እንደመጣልን መጨረሻ ማስታወቂያ ነገሩ ወደስምምነት ስለደረሰ የሚቀቡት የኢትዮጵያ ጳጳሳት በሐምሌ ፲፯ ቀን ዓርብ ከአዲስ አበባ እንዲነሱና የመቀባታቸውም ሥርዓት በሐምሌ ፲፱ ቀን እሑድ በእስክንድርያው ፓትሪያርክ እንዲፈጸም ተወስኗል ።—

ዛሬ እንድትሰበሰቡ ያደረግነው ይኸንኑ እንድትሰሙት ነው የሚል ነው ፤ ጉባኤውም ጉዳዩ በስምምነት ወደመልካም ፍጻሜ በመድረሱ የተሰማውን ደ ስ ታ ከገለጠ በኋላ በደስታ ተመለሰ ።—

ከዚህም በኋላ የጵጵስና መዓርግ ለመቀበል ካሁን በፊት የተመረጡት ብፁዓን አበው ሐ ም ሌ ፲፮ ቀን በ፲፩ ሰዓት ተኩል ከግርማዊ ጃንሆይ ተሰናብተው ሐምሌ ፲፯ ቀን በ፩ ሰዓት በአየራዊ ጉዞ ተጉዘው ወደእስክንድርያ ሔዱ ፡ ክቡራን መኳንንትና ሚኒስትሮች ፡ ሊቃውንትና መምህራን እስከ አይሮፕላን ማረፊያ ድረስ ሔደው ሸኙዋቸው ።—

የሔዱትም ቅዱሳን አበው ስማቸው ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው ።

፩ኛ / ብፁዕ እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ፡
፪ኛ / መምህር ገሪማ ፡
፫ኛ / ሊቀ ሥልጣናት መልእክቱ ፡
፬ኛ / መምህር ዘሬ ብርሃን ፡
፭ኛ / መምህር ጌታሁን ፡

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የእነዚህ ብፁዓን አበው አየራዊ ጉዞ ተቃንቶ የሔዱበትም አሳብ ተከናውኖ በደኅና ደርሰው እንዲመለሱ በኃዘንና በጸሎት ሰነበተች ።—

ምዕራፍ ፩ ክፍል ፲፯ ።

ሢመተ ጳጳሳት ኢትዮጲያውያን ፤

በአለፉት ዓመታት በልዩ ልዩ ምክንያት መሰናክል አግኝቶት የነበረውን የሁለቱን ቤተ ክርስቲያኖች ጉዳይ የግርማዊነታቸው ትጋትና ትዕግሥት መልካም ፍጻሜ እንዲያገኝ አድርጎ የስምምነቱ መፈጸም ከተረጋገጠ በኋላ አምስቱ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ብፁዕ እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ፣ መምህር ገሪማና ሊቀ ሥልጣናት መልአክቱ፣ መምህር ዘፈረ ብርሃንና መምህር ጌታሁን ሐምሌ ፲፯ ቀን ፲፱፻፵ ዓ ም ዓርብ ከጧቱ በ፮ ሰዓት ከ፲ ደቂቃ ከአዲስ አበባ ተነሥተው በኢትዮጲያ ያየር መንገድ ተጉዘው በ፲፩ ሰዓት ካይሮ ገቡ ።—

የአየሩም መንገድ በአሥመብና በሉክሶር ላይ ነበር፣ ጳጳሳቱ ካይሮ ፋሩክ ፊልድ ላይ ከአይሮፕላን ሲወርዱ በካይሮ ያሉት የኢትዮጵያ ሚኒስትር ክቡር ፊታውራሪ ታፈሰ፣ ክቡር ሳባ ሐበሺ ፓሻና ቆሞስ ኢብራሂም ሉቃስ፣ የፓትሪያርኩ መልእክተኞችና ጳጳሳት ሌሎችም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ወዳጆች ደስ በሚያሰኝ አኳኋን ተቀበሏቸው ።—

ኢትዮጵያውያኑ ጳጳሳት በተቀባዮቻቸው ታጅበው ካይሮ ከተማ እንደገቡ በመጀመሪያ ወደ በትረ ካናው ሔደው ለብፁዕ ፓትሪያርኩ ለአቡነ ዮሳብ ሰላምታ አቀረቡ፤ ፓትሪያርኩም በደስታ ተቀብለው ጥቂት ጊዜ ካነጋገሩዋቸው በኋላ ተሰናብተው በኢትዮጵያ ሊጋሲዎን ወደ ተዘጋጀው ሥፍራ ሔዱ ።—

ብፁዕ እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስና ብላታ መርስዔ ኃዘን በዚሁ ቀን ወደማታ ወደ አብዲን ቤተ መንግሥት ሔደው በጐብኚዎች መዝገብ ላይ ስማቸውን ጽፈው ተመለሱ ።—

የፓትሪያርኩ ሽልማት ፤

የኢትዮጵያ ነገሥታት ለሃይማኖት አባቶቻቸው ለእስክንድርያ ፓትሪያርኮች ሽልማት መስጠት ልማዳቸው ነው ፤

እንደዚሁ ሁሉ፤ግርማዊ ንጉሠ ነገሥታችን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለብፁዕ ፓትሪያርክ ለአቡነ ዮሳብ በጣም ደስ የሚያሰኝ ሽልማት የወርቅ ላንቃና የሥላሴን ኮርዶን ኒሻን ልከውላቸው ነበርና፤ክቡር ፊታውራሪ ታፈሰና ብላታ መርስዔ ኃዘን ይህንኑ ሽልማት ለማስረከብ፤ ሐምሌ ፲፯ ቅዳሜ በ፱ ሰዓት በቀጠሮ ወደበትረ ካናው ሔዱ ።—
በትረ ካናው በማብዕና በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ አጊጦ ነበር ።— ፓትሪያርኩም

ከጳጳሳትና ከታላላቅ ሰዎች ጋር ሆነው ተቀበሏቸው ፣ ሽልማቱን አቅርበው ባስረከቡ ጊዜ ፳፱ ዕድሜ ያደረጉት አባታችን ብፁዕ ፓትረያርክ እጅግ ደስ ስላላቸው ወዲያው ላንቃ ካባውን ለብሰው ኒሻኑን አድርገው ፎቶግራፍ ተነሡ ።

ካሁን በፊትም በ፲፱፻፳፪ ና ፳፫ ዓ ም ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ሳሉ ከግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በየጊዜው ተቀብለዋቸው የነበሩትን ኒሻኖች ባለኮርዶን የኢትዮጵያ ኮከብና የዳግማዊ ምኒልክን ኒሻን አቅርበው ለሕዝቡ እያሳዩ ደስታቸውን ገለጡ ፣ በመጨረሻውም ቡራኬ ሰጥተው አሰናበቱዋቸው ።—

አስኬማ ፣

አስኬማ ማለት በመጽሐፈ ምንኵስና ከሚገኙት ከሦስቱ የምንኵስና ማዕርጎች አንደኛው ነው ፣ ሦስቱም ማዕርጋት ቆብዕ ፣ ቅናት ፣ አስኬማ ናቸው ፣ እነዚህንም መጽሐፈ ቆብዕ ዘሠለስቱ ደቂቅ ቅናት ዘዮሐንስ መጥምቅ ፣ አስኬማ ዘኤልያስ ብሎ ይደለድላቸዋል፤ መምህራን ግን ቆብን በአክሊለ ሦክ ፣ ቅናትን በሀብለ፣ተቀሥፎ፣ አስኬማን በንጽሐ መላእክት መስለው ይናገርዋቸዋል ፣ አስኬማ ከልዝብ ባሕረ ዓረብ ፣ ተሠርቶ ትእምርተ መስቀል አልፎ አልፎ ተታቶ ይገኝበታል ። በሀገራችንም የደብረ ዳሞና የአክሱም መነኵሳት አስኬማውን ከክር፤ ወይም ከባሕር ዓረብ እያሳመሩ ይሠሩታል ።—

ሐምሌ ፲፯ ቀን ቅዳሜ ብፁዕ ፓትረያርኩ ለጳጳሳት የሚገባውን የአስኬማ ጸሎት የሚአደርሱ ስለሆነ ፣ በ፱ ሰዓት ተኩል ወደበትረ ካናው ሔደው ከዚያ ሲደርሱ የደስታ ደወል ተደወለ ፣ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት ከበር ላይ ጠብቀው ተቀበሉና ወደማረፊያው ወሰዱዋቸው ።—

ከጥቂት ደቂቃ በኋላ ፣ በልብሰ ተክህኖ ያጌጡ ፲፯ ዲያቆናት መጥተው በቀኝና በግራ ተሰለፉ ፣ ብፁዕ ፓትረያርክ ጳጳሳቱን አስከትለው ከዲያቆናቱ መካከል ሲደርሱ የኛም አባቶች እጅ ነስተው ፤ ተገናኙ ከዚያም በኋላ ዲያቆናቱ በዜማ እየዘመሩ እጅበዋቸው ወደቤተ ክርስቲያኑ ገቡ ፣ ቤተ ክርስቲያኑም በኤሌክትሪክ ብርሃን አንፀባርቆና ደምቆ ነበር ፣ የአስኬማውን ሥርዓት ለማየት የተሰበሰበውም ሕዝብ እጅግ ብዙ ነበር

ፓትረያርኩም በመንበራቸው ላይ ሆነው የአስኬማውን ጸሎት ሲጀምሩ የጵጵስና ማዕርግ የሚቀበሉት ጳጳሳት በወለሉ ላይ በወንበር ተራ በተራ ተቀመጡ ፣ ከገዳመ ሱርያን የመጣ ቴዎፍሎስ የተባለ አንድ መነኵሴ በዚሁ ቀን ጵጵስና እንዲቀበል ተደርጎ ኖሮ ከአምስቱ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ጋር ስድስተኛ ሆኖ ተቀመጠ —

ፓትረያርኩ የስድስቱን ጳጳሳት ስምና የሀገረ ስብከታቸውን ስም እየጠሩ ረጅም ጸሎት አድርገው ከባረኳቸው በኋላ ፣ አስኬማውን ለያንዳንዳቸው አጠለቁላቸው፣ አምስቱ የኛ ጳጳሳት ገና በአዲስ አበባ ሳሉ የታሰበላቸውን እነሱ ጭምር በጸሎት የመረጡት ስም ስለነበረ ለፓትረያርኩ ቀደም ብሎ ተነግሮአቸው ነበርና በዚያው ስም ሠየሟቸው ፣ ይኸውም እንደሚከተለው ነው ።—

፩ኛ / የብፁዕ እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ስም ፣ ባስልዮስ ፣
፪ኛ / የመምህር ገሪማ ስም ፣ ሚካኤል ፣
፫ኛ / የሊቀ ሥልጣናት መልእክቱ ስም ፣ ቴዎፍሎስ ፣

፬ኛ / የመምህር ዘፈረ ብርሃን ስም ፤ ያዕቆብ ፤
፭ኛ / የመምህር ጌታሁን ስም ፤ ጢሞቴዎስ ፤
የአስኬማው ጸሎት ካለቀ በኋላ ፓትረያርኩ እንደ ፊተኛው በጳጳሳትና በዲያቆናት ታጅበው ። ተመለሱ ። ኢትዮጵያውያኑም ጳጳሳት ተሰናብተው ወደማረፊያቸው ሔዱ ።—

ጵጵስና ፤

የጵጵስናው ሥርዓት ሐምሌ ፲፰ ቀን ፲፱፻፺ ዓ ም እሑድ በበትረ ካና በቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን እንዲፈጸም በፕሮግራሙ ተነግሮ ስለነበረ ፤ ሕዝቡ ከጥዋቱ በ፩ ሰዓት ጀምሮ በበትረ ካናው ምድረ ግቢ ተጀነጀነ ። በትረ ካና ማለት ፓትረያርኩ የሚቀመጡበት ሥ ፍ ራ ወይም የፓትረያርክ ግቢ ማለት ነው ። በግቢውም የቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ተሠርቶበታል ።—

ጳጳሳቱ በ፩ ሰዓት ተሩብ በበትረ ካናው ደረሱ ፤ እንደደረሱም አምስት ጳጳሳት በበር ላይ ጠብቀው ተቀበሉዋቸውና በ፩ ሥፍራ አሳረፉዋቸው ።—

ከፓትረያርኩ ቤት አንስቶ እስከ ቤተ ክርስቲያኑ ያለው ወለል በምንጣፍ አጊጦ ነበር ፤ በማረፊያውም ሥፍራ ጥቂት እንደቆዩ ፓትረያርኩ በጳጳሳት ታጅበው ዲያቆናቱ በቀኝና በግራ ሆነው በዜማ ይባቤ እያደረጉላቸው በትልቅ ግርማ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ገብተው ቅዳሴ ጀመሩ ፤ ጳጳሳቱ ግን እስኪጠሩ ድረስ በዚያው ሥፍራ ቆይተው ነበር ። ቅዳሴው በ፫ ደረጃ የተመደበ ነው ። መጀመሪያ ደረጃ ቀዳስያኑ በንዋያተ ቅድሳት ላይ የሚጸለየውንና ሌላውን የጸሎት ጓዝ የሚፈጽሙበት ነው ።—

ሁለተኛው ደረጃ የምንባባት ክፍል ይባላል ። እርሱም እስከ ፍሬ ቅዳሴ ያለው ነው ፤ ሥርዓተ ሢመት የሚያደርጉትም በዚህ ጊዜ ነው ፤ የቅዳሴው፤ጸሎት ከሁለተኛው ደረጃ በደረሰ ጊዜ በጵጵስና ልብስ ያጌጡ አምስት ጳጳሳት በአቡነ ቶማስ እየተመሩ መጥተው ኢትዮጵያውያኑን ጳጳሳት ወደቤተ ክርስቲያኑ አጅበው ወሰዱዋቸው ፤ ለባስያኑም ዲያቆናት ለፓትረያርኩ ባደረጉት ዓይነት እያዜሙ አጅበው ተከተሉ ፤ ከቤተ ክርስቲያኑ ሲገቡ ሕዝቡ በደስታ ተቀበላቸው ፤ ሴቶችም እልል አሉ ፤ የእልልታው ቃና በፍጹም እንደሀገራችን ነው ።—

አዲሶቹን ጳጳሳት በመቅደሱ በር ላይ ፊታቸውን ወደምሥዑ እ ያ ደ ረ ጉ በወንበር አስቀመጡዋቸውና ብፁዕ ፓትረያርክ ሌሎቹም ጳጳሳት መጽሐፈ ሢመቱን እያነበቡ በየተራ ብዙ ጸሎት አ ደ ረ ጉ ፤ በየጸሎቱም ፍ ጻ ሜ ፓትረያርኩ የያንዳንዳቸውን ስምና ሀገረ ስብከታቸውን እየጠሩ ሲባርኳቸው መዘምራኑ በረጅም ዜማ አ ሜ ን እያሉ ይቀበሉ ነበር ።—

በመጀመሪያው ክፍለ ጸሎት አዲሱን የጵጵስና ቆብ ባርከው ደፉላቸው ፤ በሁለተኛው ጊዜ ከአዲስ አበባ ተይዞ የሔደውን የወርቁን ካባ ላንቃ ባርከው ሲያለብሱዋቸው ሕዝቡ ላንቃውን ለማየት ውካታ ጃጃታ አደረገ ፤ የላንቃው ውበት እንግዳ ሆኖ ስለታየ ለሕዝቡ ዓይን ናፍቆትን አተረፈለት ። የሹመቱ ጸሎትና ሥርዓቱ ካለቀ በኋላ

ጳጳሳቱ ወደ መቅደስ ገቡ፤ብፁዕ ፓትረያርክ ገባሬ ሠናይ ካህን ሆነው ቅዳሴ ባስል ዮስን ቀደሱ፤በዚህም ጊዜ ሰባት የግብፅ ጳጳሳትና አምስቱ አዲስቹ ጳጳሳት ቆሞሳትና ዲያቆናት ተራዳኢያን ሆነው አብረው ቀደሱ ።—

ቅዳሴውም በ፩ ሰዓት ተኩልተፈጸመና ከቅዱስ ቍርባን በኋላ ፓትረያርኩ መስቀል ይዘው ባዲስቹ ጳጳሳት አፍ ላይ ንፍኡ መንፈስ ቅዱስ ኢየሱ በንፍሐት ሀብቶ መን ፈስ ቅዱስ አሳደሩባቸው ።—

ሠርሆተ ሕዝብ ካደረጉ በኋላም ከቤተ መቅደስ እወጣለሁ ሲሉ አዲስቹን ጳጳ ሳት ለማየት ለናፍቆት ያሰፈሰፈው ሕዝብ ከብዛት የተነሣ የማያሳልፍ ስለሆነ ወደው ስጥ ተመልሰው በአንድ የጓዳ በር ይዘዋቸው ወጡ ።—

ከደጅ ሆኖ ሲጠባበቅ የነበረው ከ፫ሺ ህ የሚበልጥ ሕዝብ ጳጳሶቻችንን ባያቸው ጊዜ እጃቸውን ለመሳለምና በረከት ለመቀበል ሲሸቀዳደምና ሲጋፋ የፍቅሩ ብዛት በጣም ያስደንቅ ነበር፤

በዚሁ ጊዜ የመንግሥት ሙዚቀኞች ተሰልፈው መጥተው ሙዚቃ መቱ፤ቀጥ ሎም የኢትዮጵያን ሕዝብ መዝሙር በሙዚቃ አሰሙና ለጳጳሳቱ ሰላምታ አቀረቡ፤ ጳጳሳቱ ወደ ፓትረያርኩ ቤት በገቡ ጊዜ ሕዝቡ እያጨበጨበና ደስታውን እየገለጠ በየቤቱ ሔደ ።—

ግብዣ፤

የሁለቱ ቤተ ክርስቲያኖች ፍቅር በመልካም መሠረት በመመሥረቱ ታላቅ ደስታ ስለሰጠ፤በትረካናው በዚሁ ቀን ስለ ኢትዮጵያ ጳጳሳት ክብር በ፯ ሰዓት ተሩብ ትልቅ ግብዣ አደረገ፤ በግብዣውም ላይ ብፁዕ ፓትረያርክና ፓሻዎች ጳጳሳትና ታላላቅ ሰዎች በድምር አምሳ ያህል ሰዎች ነበሩ ።—

ከፓትረያርኩ ግራ ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ጳጳስ ዘሸዋ ወእጨጌ ዘደብረ ሊባኖስ፤ ተቀመጡ። የቀሩት ጳጳሳት ከግብፃውያን ጳጳሳት ጋር እየተሰባጠሩ በመዓርግ ሥፍራ ተቀመጡ። በስተቀኝም በኩል ክቡር ፊታውራሪ ታፈስና ፓሻዎች፤ ብላታ መርስዔ ኃዘንና ታላላቅ ሰዎች ተቀመጡ—።

የግብዣውም ሥነ ሥርዓት ውበት ያለው ነበር። ምግቡ በያይነቱ ቀረበ። በመ ጠጥ በኩል ግን ከተጣራ ውሃ በቀር አንዳች የአልኮል ወገን ስላልቀረበ ሥነ ሥርዓቱ ደስ አሰኘ።

## በኢትዮጵያ ሌጋስዮን ፡

ሚኒስትሩ ክቡር ፊታውራሪ ታፈሰ ሀብተ ሚካኤል ሐምሌ ፲፱ ቀን ሰኞ ማታ ከአንድ ተኩል እስከ ሦስት በኢትዮጵያ ሌጋስዮን ስለ ጳጳሳቱ ክብር ለፓሻዎችና ለጳጳሳት ለአፊንዲዎችም ግብ ገባ አደረጉ ። በዚሁ ጊዜ የሁለቱ አገሮች ጥንታዊ ፍቅርና ግንኙነት በጨዋታ እየተነሣ ፍሥሐ ሆኖ አመሸ ።—

## በእስክንድርያ ፡

የቅዱስ ማርቆስ ዓፅመ ርእሱ የሚገኝበት መቃብር በእስክንድርያ ስለሆነ ፡ ይህን ቅዱስ ሥፍራ መሳለምና ከቅዱስ በረከቱ ለመሳተፍ አባቶቻችን አምስቱ ጳጳሳት ለማክሰኞ አጥቢያ ሌሊቱን ወደ እስክንድርያ ወረዱ ።—

ጡዋት በ፩ ሰዓት በትልቁ የቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን መሥዋዕት አቅርበው በኢትዮጵያዊ ሥርዓት ቅዳሴ ባስልዮስን ቀደሱ ። ከቀደሱም በኋላ ለገዳሙ እርዳታ ፴ ፓውንድ ሰጥተው ለነዳያንም ቸርነት አድርገው ወደ ካይሮ ተመለሱ ።—

## ወደ አዲስ አበባ መመለስ ፡

አባቶቻችን ብፁዓን ጳጳሳት ሐምሌ ፳ ቀን ማክሰኞ ወደ በትረካና ሔደው ከብፁዕ ፓትርያርክ ሲሰናበቱ ፡ ፓትርያርኩ ጸሎት አድርሰው ባረኩዋቸው ፡ እስከ በሩም ድረስ ዘልቀው ሸኙዋቸው ።—

ሐምሌ ፳፪ ቀን ረቡዕ በ፩ ሰዓት ከካይሮ ተነሥተው ፓርትሱዳን ላይ ጥቂት ዕረፍት አደረጉ ፡ ከዚያም ተነሥተው አሥመራ በ፯ ሰዓት ደረሱ ፤ አቢያተሩ ስለ ዓየሩ አኳኋን በአሥመራ ማደርን ስለመረጠ ሌሊቱን በአሥመራ ማሳለፍ ግድ ሆነ ፡ በዚህም ጊዜ የኢትዮጵያ ላይዘን ጸሐፊ አቶ ተክሎላ ገብረ መድኅን ተቀበሉዋቸው ፡ መጀመሪያ ወደ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ሔደው ተሳለሙ ፡ አካሔዳቸው ምንም እንኳ በድንገት ቢሆን አቡነ ቄርሎስ ወዲያው ደወል አስደውለው ወንዱም ሴቱም ተሰብስቦ በታላቅ ደስታ ተቀበሏቸው ።—

## በአዲስ አበባ የተደረገላቸው የደስታና የክብር አቀባበል ፡

እግዚአብሔር የፈቀደበት ቀን ደርሶ የልብ ተስፋ እስኪፈጸም ድረስ ሰፊ ትዕግሥትና ጽኑ ሃይማኖት ያስፈልጋል ።—

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከመንበረ ማርቆስ ያላትን መንፈሳዊ መገናኛ ሳታቋርጥ የሚገባትን መብት እንድታገኝ ከ፲፱፻፳፩ ዓ ም በፊት ጀምረው የሠሩት ሃይማኖታዊ ሥራ በእግዚአብሔር ዘንድ የተፈቀደ ሆኖ ፲፱፻፳፩ ዓ ም ኢትዮጵያ ከልጆቹዋ ጳጳሳት ለማግኘት ቻለች ።—

እነዚህም ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት እንደፋና በኢትዮጵያ ጠፈር እያበሩ ከዚያ ከጭለማ ሰዓት በደረሱ ጊዜ ፡ አቡነ ጴጥሮስና አቡነ ሚካኤል በቃላቸው የዘሩትን የሃይማኖት ተክል በደማቸው አጸደቁት ።—

ከላይ የእግዚአብሔርን ፥ ከታች የንጉሥ ነገሥትን ውለታ ለመመለስና የወገንን ኩራት ለመመሥረት ከዚህ በቀር የበለጠ መንፈሳዊ ጥበብ አይገኝም ።—

የዚህም መሠረቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሆነ ፥ የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት መንፈሳዊና ሥጋዊ ትልም እንቅፋቱን ሁሉ እያስወገደ ከዳር ለመድረስ በመቻሉ ፥ የኢትዮጵያ ምእመናን የደስታ መዝሙር ሊዘምሩና የእግዚአብሔርን ምስጋና በሰፊው ሊናገሩ ይገባቸዋል ። —

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አሳባቸው ሁሉ እውነትንና ቅንነትን የተመላ ስለሆነ ፥ ሲፈጸም እንጂ ሲቀር የታየበት ጊዜ የለም ።—

በድል አድራጊነት ተመልሰው የኢትዮጵያን ነፃነት ካረጋገጡ ወዲህ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያናችን የሚገባትን እንድታገኝ በሰፊው ሲደክሙ ከቆዩ በኋላ እነሆ ድካማቸው ዛሬ ሰማያዊ ፍሬ አስገኘ ።—

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን የሚገባትን አገኘች ፥ በሉቃስ ወንጌል በመጀመሪያው ምዕራፍ ወንጌላዊ ስለወንጌል ነገር ሲጽፍ ፥ ሊጽፉ የጀመሩ ብዙ ነበሩ፥ ለነዚያ አልቀናቸውም ፥ ለኔ ግን ቀናኝ ያለው በግርማዊ ንጉሠ ነገሥታችን ሥራዎች ሁሉ በጉልህ ታይቶአል ። ከዚህ ቀደም ሊሆኑ ያልቻሉ ሥራዎች ሁሉ ሆነዋል ።—

ይህ ሁሉ መልካም ምኞትና ሃይማኖታዊ ተስፋ ስለደረሰ ፥ ብፁዓን አባቶቻችን ወደግብፅ ተልከው በመንበረ ማርቆስ ወንበር በተቀመጡት በፓትሪያርኩ በአቡነ ዮሳብ እጅ ሐምሌ ፲፰ ቀን ተሾሙ ። ሐምሌ ፳፩ ቀን ከምድረ ግብፅ ተነስተው ሐምሌ ፳፪ ቀን በ፬ ሰዓት ተኩል አዲስ አበባ ገቡ ።

ሐምሌ ፳፪ ቀን ከጥዋቱ በ፫ ሰዓት ልዑል አልጋ ወራሽ ፥ ልዑላን መሳፍንት ፥ክቡራን መኳንንትና ሚኒስትሮች ፥ ሊቃውንትና መምህራን ታላላቅ የመንግሥት ሠራተኞች የከተማው ሕዝብ ወደ አይሮፕላን ማረፊያ ሲጎርፍ ደስታ እየተሰማው ነው ፥ ሰንደቅ ዓላማዎች ሁሉ በየመንገዱ ዳር ተሰቅለዋል ። ስለ ደስታው ሕዝቡ በየመንገዱ ዳርና በየአደባባዩ አካባቢ ተሰልፈዋል ።—

ጊዜው ዝናም ስለነበረ ሕዝቡ አልሰማውም ፥ ደስታው እንደዝናም ልብስ ሆኖት የሚመለከተው ሰማይ ሰማዩን ብቻ ነበር ።

፬ ሰዓት ሲሆን አኤሮፕላኑ አዲስ አበባ ከማረፊያው ደርሶ አረፈ ልዑል የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት አልጋ ወራሽ ወደ አይሮብፕላኑ ቀርበው ገብተው የግርማዊ ንጉሠ ነገሥትን መልካም ሐሳብ ገልጸው ተቀበሏቸው ።—

ከዚህም በኋላ ብፁዓን ጳጳሳት በወርቅ የተቃጠለና የተንቆጠቆጠ ለማዕርጋቸው የተገባ ካባ ላንቃ ለብሰው ብቅ ባሉ ጊዜ፥ በጫንቃ ቸው ላይ ያረፈው ጸጋ እግዚአብሔር የሕዝቡን ልብ በደስታ አንቀሳቀሰው ፤ ለደስታም መግለጫ የተደረገው ጭብጨባ አየሩን መላው በዚህ ጊዜ በዚያ የተሰለፉት የጦር ወታደሮች ለብፅዕናቸውና ለቅድስናቸው የተገባ ሰላ ምታ ሰጡ ።—

የብፁዓን ጳጳሳቱም የተቀብዖ ስማቸው እንደሚከተለው ነው ።

ብፁዕ እጨጌ ፥ ገብረ ጊዮርጊስ አቡነ ባስልዮስ ፥ መምህር ገሪማ አቡነ ሚካኤል ፥ ሊቀ ሥልጣናት መልእክቱ አቡነ ቴዎፍሎስ ፥ መምህር ዘፈረ ፥አቡነ ያዕቆብ ፥ ከአኤሮ ፕላን ወርደው ሕዝቡን እየባረኩ ቀርበው ሁሉም ደስታውን ከገለጹላቸው በኋላ በተ ዘጋጀላቸው አውቶሞቢሎች ሆነው በአቶ ቢስኪሊተኞች ታጅበው ወደ ታላቁ ቤተ መንግሥት ጉዞ ሲደረግ የነበረው አጀብ ያስደንቅ ነበር ።—

ከቤተ መንግሥቱም ግቢ ስለ ጳጳሳቱ ክብር የክብር ዘበኞች ተሰልፈዋል ፥ ሰንደቅ ዓላማዎች ና ልዩ ልዩ የደስታ መግለጫዎች በዚያም እየታዩ የሕዝቡን ዓይን ይስቡ ነበር ።—

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትና ግርማዊት እቴጌ ቀደም ብለው ሔደው በታላቁ ቤተ መንግሥት በተዘረጋው ዙፋን ሆነው ጥቂት እንደቆዩ ጉዞው ከቤተ መንግሥቱ ደረሰ

ከዚህም በኋላ ብፁዓን ጳጳሳት ለማረፊያ ከተዘጋጀው ከክብር ሥፍራ ጥቂት ዐረፍ ካሉ በኋላ በዋናው የዕልፍኝ አስከልካይ በኰሎኔል መኰንን ደነቀ ተጠርተው ገብተው ከግርማዊ ንጉሠ ነገሥትና ከግርማዊት እቴጌ ዙፋን ፊት ከቀረቡ በኋላ ግር ማዊ ንጉሠ ነገሥት ከዚህ በታች ያለውን ለትውልድ መሠረትና ለሃይማኖት ጽናት የሆነውን ቃል ተናገሩ ።—

የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ንግግር ።—

ከቅዱስ ማርቆስ መንበር ጋር ያላትን መንፈሳዊ ግንኙነት በታላቅ ቁም ነገር ጠብቃ በአፍሪካ መካከል የክርስቲያን ደሴት እየተባለች የኖረችው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የተገባትን ታላቅነትና ክብር እንድታገኝ ስንደክምበት የቆየነው ተፈጽሞ ሁላችንም በማየታችን ዛሬ የመላው ኢትዮጵያ ደስታ ነው ።—

በቅዱስ ማርቆስ መንበርና በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መካከል የተገኘው መልካም መግባባት ፥ ቤተ ክርስቲያኖቻችን ጐን ለጐን ሆነው የሚፈጽሙት መንፈሳዊ አገልግሎት ከፍ ያለ ፍሬ የሚሰጥ መሆኑን የሚያስተማምን ነው ፥

ይህም ለግብፅና ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያኖች ከፍ ያለ ክብር የሚ ሰጥ ሥራ በዘመናችን ተጀምሮ ስለተፈጸመና ዕድሉም ለኛና በቅዱስ ማርቆስ መንበር ለተቀመጡት ለብፁዕ አቡነ ዮሳብ ፪ኛ ስለደረሰ ፥ ይህን ምክንያት አድርገን የታላቅ አክብሮት አሳባችንን ለብፁዕ ዮሳብ ፪ኛ ስንገልጥ ደስ ይለናል ።—

የኢትዮጵያ ታላቅነትና የሥልጣኔ እድገት ከሃይማኖት ትልቅነቷ ጋር የተባበረ እንዲሆን ያስፈልጋል ።—

ሃይማኖት ከሌለበት ሥፍራ ምንም ዓይነት / ኃይል / ቢገኝ ምንም ዓይነት ሥልጣኔ ቢገኝ ሥልጣኔውም በግፍ የተሸፈነ ኃይሉም በግፍ የታወረ ይሆናል ።—

የሃይማኖትንና የበጎ ምግባርን ትምህርት ለማስፋፋት ከባድ አደራ ያለበትን ኃላፊነት ተቀብላችሁ የሐዋርያነትን ሥራችሁን ስትጀምሩ በእግዚአብሔርም ስም የምትፈጽሙትና ሰማያዊ ክብር የሚያስገኝላችሁ ሥራችሁ በመልካም እንዲከናወንላችሁ እንመኝላችኋለን ።—

ከዚህ በኋላ ከብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ጀምረው ለሁሉም ለማዕርጋቸውና ለቤተ ክርስ ክርስቲያን ማዕርግ መግለጫ የሚሆን አንበሳ ወጽአ እምነገደ ይሁዳ ሞአ ሞአ ወልደ እግዚአብሔር አምላክ ውእቱ የሚል ጽሑፍና ፪ት ሥዕለ አንበሳ ያለበት በትረ ጳጳሳትና የወርቅ መስቀል ሸለሟቸው ።—

ይህም ተፈጽሞ ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ በራሳቸውና በብፁዓን ጳጳሳት ስም ሁነው ከዚህ በታች ያለውን ቃል ተናገሩ ።—

የብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ንግግር ።

ግርማዊ ሆይ ፤

ግርማዊነትዎ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እድገትና ልዕልና በታላቅ ትጋትና ድካም ያዘጋጀው ታሪክና መታሰቢያ በተመሠረተባት በዛሬይቱ ቀን በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ና አብረውኝ ባሉት አበው ጳጳሳት ፤ በኔም በራሴ ስም ለዚህ ከፍተኛ ለሆነው መልካም ሥራዎና በጎ አድራጎትዎ አፍቀርከ ጽድቀ ወዓመፃ ጸላእከ ። በእንተዝ ቀብዐከ እግዚአብሔር አምላክከ ቅብዓ ትፍሥሕት እምእለ ከማከ ብዬ ነገሬን እጀምራለሁ ።—

ጃንሆይ ፤

ያለፉትን የአባቶችዎን ነገሥታት ታሪክ ስንመለከት ፤ ሀብተ ሥጋንና ሀብተ ነፍስን ሁለቱን አንድነት አዋህዶና አጣምሮ ሕዝብን ወደ ቀናው ጐዳና ለመምራት ዕድልና ችሎታ የተሰጠው ለግርማዊ ነትዎ ሆኖ እናገኘዋለን ።—

ስለዚህም ሕዝብዎ በሥጋው የሚበለጽግበትን ፤ በነፍሱ የሚጠቀምበትን ሁለቱን ዓለማት ለመውረስ በመሪነትዎ ጐዳና ሲጓዙ ይታያል ፤ ይልቁንም በትዕግሥትክሙ ታጠርይዋ ለነፍስክሙ እንደተባለው እምነትና ትዕግሥትን መሣሪያ አድርገው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ጋር ያላት ጥንታዊ ፍቅርና ወዳጅነት ፤ መንፈሳዊ ግንኙነት ሳይቃወስና ሳያቋርጥ የሚገባትን ነፃ መብት እንድታገኝ የነበረው ጥረትዎና ድካምዎ ሁሉ ይኸው ፍሬው ደርሶ ለሕዝብዎ በመስጠት ፤ በሃይማኖት የጸናች ተስፋ የተፈጸመላት ድል አድራጊ መሣሪያ ናት ፤ ያሉትን ንጉሠ ነገሥታዊ ንግግርዎን የሚያረጋግጥ ሆኗል ።—

ጃንሆይ ፡

አባትዎ ቅዱስ ዳዊት በዘመኑ ቤተ መቅደስን ለመሥራት ተመኝቶ ነበር ። ይህ ዕድል ለልጁ ለሰሎሞን እንጂ ለርሱ ያልታዘዘ በመሆኑ ምኞቱን በሥራ ለመግለጽ አልቻለም ።—

ግርማዊነትዎ ግን ዕድለኛ በመሆንዎ ሺህ ስድስት መቶ ዘመን ባልተደላደለ መሠረት ላይ የነበረው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መብት ፡ ዛሬ በዘመኑ መንግሥትዎ ከፍጻሜ ደርሶ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያናችን ሙሉ ክብርና መብት ባለው መሠረት ላይ ለመቆም በቃች ።—

ስለዚህ ካህናቷና ሕዝብዎ ፡ ወኮሎ በጥበብ ገበርከ ፡ በዛቲ ዕለት እሙነ ተፈጸመ ፍሥሓሃ ለቤተ ክርስቲያን እያለ የሚፈልቀው ደስታ ወሰን የለውም ።—

ጃንንሆይ ፡

ዛሬ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለራስዋ የምትከበርበትንና ልጆችዋን ምእመናንን የምትመራበት ታላቅ የብርሃን ፋና አስጨብጠዋታል ። እንግዲህ ይህ በዓዋጅ የያዘችው የብርሃን ፋና በጥንቃቄ እንዲጠበቅና ለምእመናን ልጆቹዋን በትክክል እንዲያበራ የማድረጉ ሥራ የኛ የካህናቷ የሕዝብዋም አደራና ኃላፊነት ነው ።—

ግርማዊ ጃንሆይ ፡ የተቀብዖን ሥርዓት ለመፈጸም ካይሮ በነበርንበት ጊዜ ሁሉ እዚያ የሚገኙት የሃይማኖት ወንድሞቻችን ያደረጉልንን መልካም አቀባበል በተለይም ፓትርያርኩ ብፁዕ አቡነ ዮሳብ ያደረጉልንን ያባትነትና የፍቅር አስተያየት ለግርማዊነትዎ ስንገልጽ ከፍ ያለ ደ ስ ታ ይሰማናል ።—

አምላከ ማርቆስ ጸጋውንና በረከቱን በግርማዊነትዎና በግርማዊት እቴጌ መነን ፡ በተወደዱ ልዑላን ልጆችዎ ፡በሕዝብዎም ሁሉ አሳድሮ ለኢትዮጵያ ልማትና ለሕዝቧ ደኅንነ ት ፡ ለመንግሥቷ ጽንዓት እንዲሰጥልን ።—

እኛም በእግዚአብሔር ቸርነት በግርማዊነትዎ ትጋት ለበቃነው መንፈሳዊ ማዕርግ የተገባን እንድንሆን ፡ ደግሞም ለቤተ ክህነትና ለቤተ መንግሥት ኅብረታዊ ምልክት እንዲሆነን ከግርማዊነትዎ የተቀበለው በትረ ክብር ለምናደርገው መንፈሳዊ ተጋድሎ በትረ መዊዕ ሆኖልን ፡ ረዓይኪ አባግዕየ የተባለውን አምላካዊ ትእዛዝ ፈጻሚዎች በመሆን ሕዝብዎን በጸሎት ለመርዳት እሐቲ ቤተ ክርስቲያንን ለማገልገል እንድንበቃ ሁሉን የሚችለውን እግዚአብሔርን እንለምናለን ።—

ንግግሩ እንደተፈጸመ ፳፫ ጊዜ መድፍ ተተኩሰ ይህ ም ለክብራቸው ከመደረጉ በላይ የሐዋርያነታቸውን ቃለ ፀዋዲ የሚገልጽ ሥራ መሆኑ ለሕሊና ይሰማ ነበር ፤ ከዚህ ም በኋላ የሻ ምፓኝ ግብዣ ተደረገና ተሰነባብተው ጉዞ ወደ አቡነ ጴጥሮስ ሐውልት ቀጠለ።

## ክፍል ፲፯ ።
## በበዓል ላይ በዓል

ቀኑ ሐምሌ ፳፪ ቀን በመሆኑ የኢትዮጵያዊውን ሰማዕት የአቡነ ጴጥሮስ ዕረፍት መታሰቢያ ስለነበረ ጳጳሳቱ በክብር አጀብ ተጉዘው በአቡነ ጴጥሮስ ሐውልት ሥር የአበባ አክሊል አስቀመጡ፥የጴጥሮስ የደሙ ድምፅ ወደ እውነተኛው ፈራጅ ደርሶ የ ኢትዮጵያ መን

ፈሳዊ ሥጋዊ ሕይወት ታድሶ በዓለ ዕረፍቱ ከዳግማዊ በዓለ ሢመቱ ጳጳሳት ተባብሮ ሲከበር ማየት የድንቅ ድንቅ ነበር ፤ ከጳጳሳቱም አምስቱ አዲሶች ሲሆኑ ስድስተኛው አብረዋቸው የተሾሙት አቡነ ይስሐቅ በመሆናቸው የቤተ ክርስቲያን ሕይወት ትናንትናም ዛሬም የማይለወጥ መሆኑ ታይቶአል ሐምሌ ፳፫ ቀንም እንደገና በብዙ ሺህ የሚቆጠር ሕዝብ በተሰበሰበበት ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መሳፍንትን መኳንንትን አስከትለው በተገኙበት በመናገሻ ቅዱስ ጊዮርጊስ ከፍ ያለ በዓል ተደርጎአል። ከየአድባራቱ የመጡ ካህናት ከሌሊቱ ጀምረው ማኅሌቱን ሲያከናውኑ ዋሉ በአራት ሰዓት ተኩል ብፁዓን ጳጳሳት በክብር ታጅበው ከመናገሻ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ደረሱ ፤ ወደ ቤተ መቅደሱም ገብተው ጸሎተ ሕሊና ሲያደርሱ እንደ ቆዩ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ልዑል አልጋ ወራሽን አስከትለው በሞተር ቢስክሌተኞች ታጅበው ከቤተ ክርስቲያን ደረሱ ፤ ወደ ውስጥም ገብተው ጸሎተ ሕሊና ካደረሱ በኋላ ታቦቱ ወጥቶ ዑደት ተደረገ ፡ በዑደቱ ላይም ህየንተ እበውኪ ተወልዱ ለኪ ደቂቅ ወትሠይሚዮሙ መላእክተ ለኩሉ ምድር ወይዘከሩ ስመኪ በኵሉ ትውልደ ትውልድ የሚለው ምስባክ ተሰበከና ከዮሐንስ ወንጌል ም ፲ ተነበበ ። ከዑደቱ ፍጻሜ በኋላም ጸሎተ ቅዳሴው በብፁዓን ጳጳሳት ተከናውኖ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ወደ ቤተ መንግሥታቸው ፤ ብፁዓን ጳጳሳትም ወደ ማረፊያቸው ሲመለሱ የበዓሉ ፍጻሜ ሆነ ።—

## ምዕራፍ ፲፩ ክፍል ፲፰ ።

## ሊቀ ጵጵስና ፤

ምንም እንኳ ሊቀ ጵጵስና ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ቢሾሙም ፡ የእስክንድርያው ፓትሪያርክ የወደደውን ይሹምላቸው እንጂ የኢትዮጵያ ሰዎች ከአዋቂዎቻቸው ሊቀ ጳጳሳት አይሹሙ ፤ ያውም ቢሆን በስም ሊቀ ጳጳሳት በመባል ብቻ ይክበር እንጂ ጳጳሳትን ሊያጰጵስ አይገባውም የሚለው ኀደብ እስከ ተጣሰና አሳዛኙ ሰው ሠራሹ ግንብ እስከ ፈረሰ ድረስ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ መብት ጉዳይለሚሰማ ፤ ለሚያይ ፡ ለሚያስተውል ሕሊና ዕረፍት የማይሰጥ ስለሆነ ሰላማዊው መሪ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የሰላም ትግላቸውን አላቋረጡም ።

ስለዚህም ጉዳዩ በውይይት ቆይቶ የኢትዮጵያው ሊቀ ጳጳሳት ግብጻዊው አቡነ ቄርሎስ ባሉበት መብታቸው ተጠብቆላቸው ቆይተው ጥቅምት ፲፪ ቀን ፲፱፻፵፫ ዓ ም ካረፉ በኋላ በዚሁ ዓ ም ጥር ፮ ቀን ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ካይሮ በሚገኘው በቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ከእስክንድርያው ፓትሪያርክ ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ዮሳብ መዓርገ ሊቀ ጵጵስና ተቀብለው የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ሆኑ ።

በዚህ ጊዜ ጃንሆይ የፈጸሙት መንፈሳዊ ተግባር ለሁለቱ ሀገሮች ለእስክንድርያና ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታላቅ ውለታ ሠርቶአል ፡ እስክንድርያና ኢትዮጵያ ባልተመጣጠነ የሥልጣን ይዞታ ሺ ስድስት መቶ ዓመት ሲኖሩ እያደር እየሠፋ የሄደ ቁስል ታይቶአል ፡ ኢትዮጵያውያን ቅዱስ ፍሬ ምናጦስን መርጠው ለሥልጣነ ክህነት ወደ እስክንድርያ ሲልኩት በፈቃዳቸው ነው እንጂ ሌላ ምክንያት አልነበረበትም ፤ ቅዱስ ፍሬ ምናጦስም ወደ ኢትዮጵያ እንደተመለሰ ሊቀ ካህናቱ እንበረምን ሕዝበ ቀድስ ብሎ በመ

ሾሙ የኢትዮጵያ መብት የማይደፈር መሆኑን አሳይቶአል ፡ አባቶቻችን ግን ባለቤቱ ከፍ በል ይበልህ እንጂ ፡ አንተ ራስኽ ልቀመጥ አትበል በሚለው ፡ ትምህርት ትሕትና ተመርተው ፤ በቅተው ሳሉ የአልበቁ መስለው፤ በክርስትና የበላይ፤ የበታች አለመኖሩን ሲያውቁ ራሳቸውን ለትሕትና አስገዝተው፤የቅዱስ ማርቆስን አባትነት በፍቅር ጠብቀው አፍሪቃዊነቱንም የጋራ መሆኑን ተመልክተው ሊቀ ጳጳሳትን ከግብፅ ሲቀበሉ ኖሩ ሆኖም የባቶቻችን ትሕትና ዋጋ አላጣም፡ ስለዚህም እነአቡነ ተክለ ሃይማኖት በእግዚአብሔር ቃል የሐዋርያነትን መዓርግ ሲያገኙ እግዚአብሔር ለሥራቸው የተአምራት ምስክር እየ ሰጠ ከሐዋርያነት መዐርግ መድረሳቸውን በጸጋው ያረጋገጠላቸው ብዙ ቅዱሳን ተገኝተ ዋል፡ ይሁን እንጂ ይህ ጳጳሳትን ከሌላ የመቀበል ጉዳይ በተቀባዮቹ ላይ እንደሞኝነት ሲቆጠር በሰጭዎቹ ዘንድ የትዕቢት ጠንቅ ታይቶበታል ጃንሆይ ይህንንጉዳይ በሰላማዊ ዘዴ ፍጻሜ በማድረሳቸው ተቀባዮቹን ከጸጸት ፡ ሰጭዎቹንም ከትዕቢት ፈውሰዋቸዋል ፤ ይፀም የሊቀ ጵጵስና ሥልጣን ጳጳሳትን ለመሾም የተከለከለውን ያህል እድገቱ ጨምሮ ከፓትረያ ርክነት ደርሶ ሊቃነ ጳጳሳትን ለመሾም አበቃ ፤ ብፁዕ ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ባስልዮስ ፤ ብፁዕ ወቅዱስ ፓትረያርክ ተብለው የኢትዮጵያ ፓትረያርክ ሲሆኑና በካይሮ በቅዱስ ማር ቆስ ቤተ ክርስቲያን ከእስክንድርያ ፓፓና ፓትረያርክ ከብፁዕ ወቅዱስ ኢቡነ ቄርሎስ ሳድሳዊ አክሊለ ክብር ተቀብለው ሹመቱ ሲታወጅ የአበው ተስፋ ተፈጸመ ፤ በረከት ቆመ ፲ሚና ተ፲ሚ፤ ሰጭና ተቀባይ እኩል ሆኑ ፤ መከባበር ተጀመረ ፤ መነቃቀፍ ተሻረ በኃይለ ሥላሴ ሁሉም ተገኘ ።

ከዚህ ቀጥሎ ከላይ እንደ ጠቀስነው ሁሉ ከ፲፱፻፵፫ ዓ ም እስከ ፲፱፻፳፫ ዓም የተ ፈሙ ንግግሮችና ልዩ ልዩ ጽሑፎች ተራቸውን ጠብቀው ስለሚገኙ በጥንቃቄ እንመልከት

የመጀመሪያው ኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት መሾም ።

ቦ ጊዜ ለኵሉ « ለሁሉ ጊዜ አለው ብሎ ሰሎሞን እንደተናገረው ያለፉት ነገሥታ ትና ሕዝባቸውም ይመኙት የነበረው ቅዱስ ምኞት ወደመጨረሻው ግብ ደርሶ የመፈጸሙ ዕድል ለግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በዘመናቸው ለሚገኘው ትውልድ ሆነና የኢ ትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ራስዋን የምትችልበት ጊዜ ደረሰ ፤ በ፲፱፻፵፫ ዓ ም በኢትዮ ጵያና በግብጽ ቤተ ክርስቲያን መካከል የተደረገው ስምምነት በቤተ ክርስቲያን ሕግ ጳጳስ እንደ ሥጋዊ ሹመት መዘዋወር ስለማይገባው የፊተኛው ሊቀ ጳጳስ አቡነ ቄር ሎስ የስም ሥልጣናቸውን ይዘው እንዲቆዩ በእስክንድርያ ከተቀቡት ጳጳሳት ውስጥ አንደኛው ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ የኢትዮጵያን ሊቀ ጳጳስ መንበር በእንደራሴነት እን ዲጠብቁ ከአቡነ ቄርሎስ ዕረፍት በኋላ ኢትዮጵያዊ ሊቀ ጳጳስ ተመርጦ በእስክንድርያ ፓትረያርክ እንዲሾምና እሱም ጳጳሳትን የመሾም ሥልጣን እንዲሰጠው ነበር ።

በጥቅምት ፲፪ ቀን ፲፱፻፵፫ ዓ ም የፊተኛው ሊቀ ጳጳስ አቡነ ቄርሎስ ታመው ማረፋቸው ተሰማ ፤ የኢትዮጵያም ቤተ ክርስቲያንና ምእመናንዋም ስለ ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ ሞት ኃዘናቸውን ከገለጡ በኋላ ከስድስቱ ኢትዮጵያውያን መካከል አንድ ሊቀ ጳጳስ ለመሾም ም ርጫ ለማድረግ ተወሰነ ።—